# መጽሔተ ተልእኮ



ሰኔ ፳፻፲፯

፺ኛ ዕትም

ይናገራል ፎቶው





ዲያቆን ደረጀ ጋረደው


አዘጋጅ
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት
ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን
የሕዝብ ግንኙነትና ትብብር አገልግሎት ማስተባበሪያ

# ማውጫ


01 መልእክት ዘማኅበረ ቅዱሳን
ለቤተ ክርስቲያን መሪ ዕቅድ መሳካት

02 ትምህርተ ወንጌል
“ወደ እርሱ ቅረቡ፤ ያበራላችሁማል”

03 ኪነ ጥበብ
ጾም

04 ግብረ ማኅበረ ቅዱሳን
የማኅበረ ቅዱሳን ስብከተ ወንጌል እና ሐዋርያዊ አገልግሎት

05 ቤተ እናግድ
የማኅበረ ቅዱሳን ድጋፍ ለቅዱሳት መካናትና ለአብነት ትምህርት ቤቶች

06 ይናገራል ፎቶው

# 1. መልእክት ዘማኅበረ ቅዱሳን

## ለቤተ ክርስቲያን መሪ ዕቅድ መሳካት የድርሻችንን እንወጣ!

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ ምእመናን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ወንጌል በማወቅ እንዲኖሩ በማድረግ ላይ ትገኛለች፡፡

ቤተ ክርስቲያን በዓለም መድረክ ምሳሌ ከምትሆንባቸው በርካታ ተግባራቶቿ መካከል አንዱ ጠንካራ መዋቅሯ ነው፡፡ ከቅዱስ ሲኖዶስ ጀምሮ እስከ አጥቢያ የአገልግሎት ክፍሎች ድረስ ተዘርግተው በቃለ ዐዋዲ በተቀመጠላቸው የሥራ ድርሻ መሠረት ውጤታማ ተግባራትን እያከናወኑ የሚገኙት እነዚህ መዋቅሮች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በየትኛውም የዓለም ክፍል ላይ በቀላሉ ምእመናንን ተደራሽ እንድታደርግ ረድቷታል፡፡

ይሁን እንጂ ይህች ታላቅ ቤተ ክርስቲያን በርካታ ተግዳሮቶች አሉባት፡፡ ይኸውም ከውጭና ከውስጥ ሲሆን ከውጩ ይልቅ የውስጥ ተግዳሮቶቿ ከጊዜ ጊዜ እየበዙ መጥተዋል፡፡

በርካታ መንፈሳዊና ቁሳዊ ሀብት ያላት ታላቅ ሰማያዊት መንግሥት ብትሆንም ዘመኑን የዋጀና በመሪ እቅድ ያልተደገፈ የአስተዳደር ዘይቤ ለችግሩ ቅድሚያ የሚሰጠው ነው፡፡ ዕቅድ እንኳንስ ይህችን ታላቅ ተቋም ቀርቶ ግለሰብም ቤቱን ያለ እቅድ የሚመራው ከሆነ ችግር ይከሰታል ቤት ይፈርሳል ቤተሰብ ይበተናል፡፡ ስለዚህ

ዓለም እየደረሰበት ካለው ዘመናዊነት እና እየተቀየረ ካለው የሰዎች የአኗኗር ሁኔታ አንፃር የቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር ሥራም ዘመኑን የዋጀ እና የምእመናንን የዕውቀት፣ የኑሮ እና የማኅበራዊ ሕይወት እንቅስቃሴ ከግምት ውስጥ ያስገባ ቤተ ክርስቲያኗና ምእመናንና ልጆቿን ሰማያዊ ተልእኮዋን እንዲወጡ፣ እርሷም የፈተና ማዕበሉን የምታልፍበት፣ ችግሯን የምትፈታበት፣ ሐዋርያዊ ተልእኮዋን የምትወጣበት፣ ተከባሪ፣ ተገዳዳሪና ተፈሪ ተቋም ሆና እንድትዘልቅ የሚያግዛት መሪ ዕቅድ ያስፈልጋት ነበር፡፡

በዚህ መነሻነት ጊዜው ደርሶ ፈቃደ እግዚአብሔር ሆኖ ለመጀመሪያ ጊዜ በሚባል ሁኔታ የቤተ ክርስቲያን የ፲ ዓመት መሪ ዕቅድ ጸድቆ ለባለድርሻ አካላት ሁሉ ግንዛቤ ፈጠራው እየተከናወነ ይገኛል፡፡
ዕቅድ ብቻውን ችግር አይፈታም፤ ከፉ ቀንን አያሻግርም፤ የቤተ ክርስቲያንንም መጻኢ ዕድል አይወስንም፡፡ ዕቅድ ተርጓሚ ፈጻሚ አካል ይፈልጋል፡፡ እናም ይህንን ትልቅ ተስፋ የተጣለበት መሪ ዕቅድ አፈጻጸሙን ለቤተ ክህነቱ ብቻ ትቶ ለውጥ እንዲመጣ መጠበቅ ተገቢ አይደለም፡፡

በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ባለድርሻ አካላትን ርብርብ የሚጠይቅ ነው ብሎ ማኅበረ ቅዱሳን ያምናል፡፡

የሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት፣ ማኅበራት ማኅበረ ቅዱሳንን ጨምሮ፣ በውጭም በውስጥም ያሉ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ልጆች ምእመናን በግልም በቡድንም ለዚህ መሪ ዕቅድ አፈጻጸም የማይተካ አበርክቶ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

ማኅበረ ቅዱሳን በስልታዊ ዕቅዱ አካቶና የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን መሪ ዕቅድ ግምት ውስጥ አስገብቶ የቤተ ክርስቲያንን ልእልና ሊያስጠብቅ የሚችል ሥራ እየሠራ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በቂ ነው ተብሎ የማይታሰብ በመሆኑ ግንዛቤ ፈጠራው ላይ፣ ከባለድርሻ አካላትና ተባባሪ አካላት ጋር ያለውን ቅንጅት በማስፋት፣ ከቤተ ክህነቱና መሰል ተቋማት ጋር በቅርበት በመሥራት፣ በሀገር ውስጥም ከሀገር ውጭም ባሉት የማዕከላትና ወረዳ ማዕከላት ግንኙነት ጣቢያዎችና ግቢ ጉባኤያት ሁሉ የቤተ ክርስቲያንን የ፲ ዓመት መሪ ዕቅድ ለማሳካት ያልተቆጠበ ጥረት እንደሚያደርግ እናምናለን፡፡

ሌላው ሰንበት ትምህርት ቤቶችና አንድነታቸው፣ በቤተ ክርስቲያን በልዩ ልዩ ማኅበራት የተደራጁ ሁሉ ዕቅዱን ከመረዳት እስከ ማስረዳት ከመፈጸም እስከማስፈጸም ግዴታቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡ መሪ ዕቅዱ ቅዱስ ሲኖዶስ በወሰነው መሠረት ለሚቀጥሉት ፲ ዓመታት እንዲያገለግል ተደርጎ በ፳፻፲፮ ዓ.ም ወደ ሥራ መግባቱ የሚታወቅ ሲሆን ፲፮ ግቦችን በውስጡ የያዘ እና በሁለት ዘርፎች የተከፈለ ነው ፡፡

የመጀመሪያው ዘርፍ ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ አገልግሎቶች ዙሪያ የምታከናውናቸውን ተግባራት ለማጠናከር የሚያስችሉ ፰ (ስምንት) ግቦችን የያዘ ሲሆን ሁለተኛው እና ተመሳሳይ ፰ ግቦችን የያዘው ክፍል ደግሞ የቤተ ክርስቲያናችንን የማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ቴክኖሎጂያዊ እና ተቋማዊ አገልግሎቷን ለማጠናከር የተዘጋጀ ነው፡፡

ይህ መሪ ዕቅድ ቤተ ክርስቲያንን ወደ ተሻለ የአስተዳደራዊ አገልግሎት የሚያሸጋግር በመሆኑ ከላይ የጠቀስናቸውም ያልጠቀስናቸውም ሁሉም አካላት ለተግባራዊነቱ መረባረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ቀድሞ እንደተገለጸው ዕቅድ ማቀድ ብቻውን ውጤት አይደለም፡፡ ተግባራዊነቱን ለማረጋገጥ ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ጀምሮ እስከ ቤተ ክርስቲያን የታችኛው መዋቅር ድረስ ያለን አካላት እንደየድርሻችን ውጤታማ ሥራዎችን ማከናወን ይገባናል፡፡

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር!!**

# 2. ትምህርተ ወንጌል

**“ወደ እርሱ ቅረቡ፤ ያበራላችሁማል”**
**(መዝ.፴፫፥፭)**

ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት ይህንን ኀይለ ቃል የተናገረው ስለ ሕዝቅያስ ነው፡፡ ሕዝቅያስ በሁለቱ ነገድ በነገደ ይሁዳ እና በነገደ ብንያም የነገሠ ንጉሥ ነው፡፡ በኢየሩሳሌም ያሉ ሕዝቡና ካህናቱ ከንጉሡ በቀር ጣዖት እያመለኩ፣ ኀጢአት እየሠሩ እግዚአብሔርን ቢያሳዝኑ የአሶር ንጉሥ ሰናክሬም ኢየሩሳሌምን እንዲያጠፉ ታዝዞ መላእክት በነጭ በግ አምሳል እየመሩ አመጡት፡፡ ነገር ግን ሰናክሬም ለኪሶን ሲደርስ በትዕቢትና በትምክህት መልእክተኞችን ወደ ሕዝቅያስ ልኮ ከእጄ የሚያድንህ ጣዖት አለን? ብሎ እግዚአብሔርን ተሳደበ፡፡ ሕዝቅያስም ጠላቱን ይመልስለት ዘንድ ማቅ ለብሶ፣ አመድ ነስንሶ በጸሎት፣ በምህላ ወደ እግዚአብሔር ቀረበ፡፡

በዚህም ምክንያት የኢየሩሳሌምና የሕዝቦቿ ሊሆን የነበረው ጥፋት ወደ ሰናክሬምና ወደ ሠራዊቱ ተመልሷል፡፡ ስለዚህ ንጉሡ ሕዝቅያስ “ወደ እግዚአብሔር በመቅረብ ከመከራ እንደ ዳነ እናንተም ትድናላችሁ” ለማለት ነቢዩ ዳዊት በሕዝቅያስ ተገብቶ (ስለ ሕዝቅያስ ሆኖ) ኀሠሥክዎ ለእግዚአብሔር ወተሰጥዎኒ ወእምኵሉ ምንዳቤየ አድኀነኒ ቅረቡ ኀቤሁ ወያበርህ ለክሙ እግዚአብሔርን ፈለግሁት፤ እርሱም መለሰልኝ፤ ከመከራዬም ሁሉ አዳነኝ፡፡ ወደ እርሱ ቅረቡ፤ ያበራላችሁማል” አለ፡፡
ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ምንድን ነው?

እግዚአብሔር ከበርባሮስ በታች፣ ከጽርሐ አርያም በላይ፣ ከአድማስና ከአድማስ በአፍአ (ከምድር ዳርቻዎች ውጭ) የሚኖር፣ እንዲሁም ፍጥረት ባለበት ሁሉ በምልአት የሚኖር አምላክ ነው፡፡ መዝሙረኛው ዳዊት በሌላኛው የመዝሙሩ ክፍል **«አይቴኑ አሐውር እመንፈስከ ወአይቴ እጐይይ እምቅድመ ገጽከ እመኒ ዐረጉ ውስተ ሰማይ ህየኒ አንተ ወእመኒ ወረድኩ ውስተ ቀላይ ህየኒ ሀሎከ ወእመኒ ነሣእኩ ክንፈ ከመ ንስር ወሰረርኩ እስከ ማኅለቅተ ባሕር ህየኒ እዴከ ትመርሐኒ ወታነብረኒ የማንከ ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወደየት እሸሻለሁ? ወደ ሰማይ ብወጣ አንተ በዚያ አለህ፤ ወደ ጥልቁም ብወርድ አንተ በዚያ አለህ፡፡ እንደ ንስርም ክንፍ ቢኖረኝ እስከ ባሕርም መጨረሻ ብበር በዚያ እጅህ ትመራኛለች፤ ቀኝህም ታኖረኛለች» በማለት ይነግረናል፡፡** (መዝ.፻፴፰፥፲)

እግዚአብሔር ከምልአቱ የተነሣ በሲኦል አለ፤ በእርሱ ዘንድ ግን ጨለማ የለም፡፡ ረድኤቱም በሲኦል አይገኝም፡፡ የሌለበት ቦታ የለም፤ ሆኖም ግን ኀጢአትን የሚጸየፍ አምላክ ነውና ኀጢአት ባለበት በዚያ በረድኤት ይገለጥ ዘንድ ፈቃዱ አታገብረውም፡፡ እርሱ በሁሉ እየኖረ ሁሉንም አይቀርብም፡፡ በሁሉ እያለ የማይፈቅደውን ይርቃል፤ በሁሉ እያለም የሚወደውን ይቀርባል፡፡ ከምልአቱ በጸጋ፣ በበረከትና በረድኤት ይገለጣል፤ ከምልአቱም ጸጋውን፣ ረድኤትና በረከቱን ያርቃል፡፡ ይህንን ከእርሱ በቀር ሊያደርገው የሚችል ፍጥረት የለም፡፡ ፍጥረት በምልአት ከወደደው ቦታ ደርሶ በወደደው መታየትና መገለጥ አይችልምና፡፡ ታዲያ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ምንድን ነው? ነቢዩ ወደ እርሱ ቅረቡ ያበራላችሁማል ብሎ የነገረንስ ለምንድን ነው? ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ማለት የእግዚአብሔርን ሕግ መጠበቅ፣ እርሱን ማምለክና ፈቃዱን በመፈጸም የእርሱ ማደሪያ መሆን ነው፡፡

“ያበራላችሁማል” ማለቱም የረድኤቱን ብርሃን ያበራላችኋል ሲል ነው፡፡ ይህም ወደ እግዚአብሔር የመቅረብ ዋጋው ምን እንደ ሆነ በግልጥ የሚያስረዳ ነው፡፡ እንዴት ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እንዳለብንና የምናገኘው ዋጋ ምን እንደሚሆን በሚቀጥለው አርእስት እንመለከታለን፡፡

## ወደ እግዚአብሔር እንዴት መቅረብ እንችላለን?

### ፩. በሃይማኖት

ወደ እግዚአብሔር ከምንቀርብባቸው መንገዶች አንዱ ሃይማኖት ነው፡፡  ግእዛን ያላቸው ፍጥረታት ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኙበት መንገድ ማለት ነው፡፡ ይህም ሃይማኖት ወደ እግዚአብሔር የመቅረቢያ መንገድ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ እግዚአብሔር መላእክትን ፈጥሮ ከተሰወራቸው በኋላ <<መኑ ፈጠረነ ወሚመ በበርእስነኑ ተፈጠርነ>> ማን ፈጠረን? ከወዴትስ መጣን? እርስ በእርሳችን ተፈጣጠርን? ብለው ሲመራመሩ ከሁሉም መላእክት ይልቅ በቦታም፣ በመዓርግም ከፍ ብሎ ተፈጥሮ የነበረው ዲያብሎስ እኔ ፈጠርኋችሁ አለ፡፡ በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር አምላካችን ይህ ስሑት ፍጥረት ጨርሶ ሳያስታቸው ብሎ << **ለይኩን ብርሃን**>> (**ዘፍ.፩፥፫**) ብርሃን ይሁን በማለት እራሱን በብርሃን አምሳል ለመላእክት ገልጦላቸዋል፡፡ <<**ወዝንቱ ብርሃን ኮኖሙ ጥበበ ወአእምሮ**>> **እንዲል! ይህ ብርሃን ዕውቀትና ጥበብ ሆኗቸው፣ አንድነትና ሦስትነት ተገልጦላቸው ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ብለው አመስግነውታል፡፡ (መጽሐፈ አክሲማሮስ ዘእሑድ ክፍል ፫)** ይህ የእግዚአብሔር መገለጥ ሃይማኖት ይባላል፡፡ ይህም እግዚአብሔር ከመላእክቱ ጋር የተገናኘበት፣ መላእክትም እርሱን ያወቁበትና ከእርሱ ጋር የተገናኙበት (የቀረቡበት) ነው፡፡ በመሆኑም ሃይማኖት ፍኖተ እግዚአብሔር (የእግዚአብሔር መንገድ) ይባላል፡፡

አዳም ዕፀ በለስን አትብላ ብሎ ሕግ ሲሰጠው፣ ሰባት ዓመት በገነት በዘባነ ኪሩቤል ሆኖ እየተመሰገነ ሲገለጥለት፣ ሕጉን አፍርሶ ዕፀ በለስን በበላ ጊዜም አዳም ሆይ! ወዴት አለህ? በማለት በገነት እየተመላለሰ ሲጠይቀው የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር፣ እግዚአብሔርም ከሰው ልጅ ጋር የሚገናኙበትን መንገድ አሳይቷል፡፡ (ዘፍ.፫፥፫-፲) ይህም የመገለጥ ሃይማኖት ነው፡፡ ከገነት ከወጣ በኋላ እርሱ በወደደው መጠን እየተገለጠ፣ በነቢያትና በካህናት ላይ እያደረም ተስፋውን መንገሩም ሃይማኖት የፍጡርና የፈጣሪ መገናኛ መንገድ መሆኑን የሚያስረግጥልን እውነት ነው፡፡ <<**ዘመርሖ ለአብርሃም**>> **አብርሃምን የመራው ... ተብሎ እንደ ተጻፈ፡፡ (ሃይ አበ ፺፥፱)** ይህም ፍኖተ ሃይማኖትን የመራው ማለት ነው፡፡ ስለዚህ የሰው ልጆችም ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡት በሃይማኖት መሆኑን በሚገባ እንረዳለን ማለት ነው፡፡

የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜም ቃል ሥጋ ሆኖ የሰውን ልጅ ሊፈልገው ወደዚህ ዓለም መምጣቱ የመገለጥ ሃይማኖት የሰው ልጅ ከፈጣሪው ጋር የሚገናኝበት መንፈሳዊ መንገድ መሆኑን በጉልህ ያስገነዝበናል፡፡ ለዚህም ነው «**እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በመንገድ ላይ ቁሙ፤ ተመልከቱም፤ የቀደመችውንም መንገድ ጠይቁ፤ መልካሚቱ መንገድ ወደየት እንደ ሆነች ዕወቁ፤ በእርስዋም ላይ ሂዱ፤ ለነፍሳችሁም መድኃኒት ታገኛላችሁ፤ እነርሱ ግን አንሄድባትም አሉ» ተብሎ የተጻፈው፡፡** (ኤር.፮፥፲፮) ስለዚህ ሃይማኖታችንን ጠንቅቀን በመማር፣ በመመርመርና በማወቅ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ አለብን፡፡ ያለ ሃይማኖት ወደ እግዚአብሔር መቅረብ አንችልም፤ ያለ እግዚአብሔርም ዘለዓለማዊ ድኅነት የለምና፡፡

## ፪. በጸሎት

ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበት ሁለተኛው መንገድ ጸሎት ነው፡፡ ጸሎት ማለት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ማለት ነው፡፡ (ፍት.ነገ.አን. ፲፬) ጸሎት ሦስት ወገን ነው፡፡ ይህም ጸሎተ ሥጋ፣ ጸሎተ ነፍስ፣ ጸሎተ ልቡና ነው፡፡ ጸሎተ ሥጋ በአንሳሕስሆ ከናፍር (በከንፈር ንቅናቄ) የሚደረግ ሲሆን በወጣኒነት መዓርግ ያሉ የሚጸልዩት የጸሎት ክፍል ነው፡፡ ወጣንያን ሲጸልዩ ከንፈራቸው ይንቀሳቀሳል፤ እጃቸው የሰውነታቸውን ክፍሎች ይዳስሳል፤ እግራቸው በድካም ይዝላል፡፡ ከምሥጢሩ ላይ ሳይሆን ከንባቡ ላይ ብቻ ያተኩራሉ፡፡ ጸሎተ ነፍስ ያለ አንሳሕስሆ ከናፍር (ያለ ከንፈር ንቅናቄ) ያለምንም የሰውነት እንቅስቃሴ በንጽሐ ነፍስ ያሉ ማእከላውያን የሚጸልዩት ጸሎት ነው፡፡ ንባቡን ከምሥጢሩ በልቡና እያደመጡ ይጸልዩታል፡፡ ከአፋፍ ላይ ነፋስ ከአንደበት ላይ እስትንፋስ እንደሚባለው ከዚህ መዓርግ ደርሰው የሚጸልዩ ጻድቃን ሃያ ዐራት ሰዓት ከልቡናቸወው ጸሎት ሳይለያቸው ያለ ዕረፍት የሚጸልዩ ናቸው፡፡ **<<እባርኮ ለእግዚአብሔር በኵሉ ጊዜ ወዘልፈ ስብሐቲሁ ውስተ አፉየ>> እግዚአብሔርን ሁልጊዜ አመሰግነዋለሁ፤ ምስጋናውም ዘወትር በአንደበቴ ነው እንዲል፡፡** (መዝ.፴፫፥፩) ጸሎተ ልቡና ካልደረሱበት አይታወቅም፡፡ (አንክሮና ተመስጦ ነው፡፡) ይህም በጸሎት ምን ያህል ከእግዚአብሔር ጋር መንፈሳዊ አንድነት እንደሚኖረንና ወደ እርሱ እንደ ምንቀርብ የሚስረዳን ነው፡፡ ከላይ እንዳልነው ጸሎት ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበት መንፈሳዊ መንገድ ነውና፡፡

ሕዝቅያስ እግዚአብሔርን የፈለገው፣ በአምልኮት ነው፡፡ የአምልኮት መገለጫው ጸሎት ነው፡፡ በጸሎት ለመነው፤ እግዚአብሔርም ጸሎቱን ሰምቶ ከመከራ አዳነው፡፡ ነቢያት፣ ሐዋርያት፣ ሊቃውንትና መነኰሳት በጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር አፍ ለአፍ ተነጋግረዋል፡፡ ስለዚህ እኛም አባቶቻችንን አብነት አድርገን ወደ አምላካችን በንጹሕ ልብ ሆነን በመጸለይ ወደ እርሱ መቅረብ ይገባናል፡፡

## ፫. በዐቂበ ሕግ

ሌላኛው ወደ አምላካችን የምንቀርብበት ዐቂበ ሕግ (ሕግን መጠበቅ) ነው፡፡ ሕጉን ስንጠብቅ በረድኤት ይቀርበናል፡፡ ማደሪያ ዞፋኑም ያደርገናል፡፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለቅዱሳን ሐዋርያት ሲያስተምር «ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለ የሚጠብቀውም የሚወደኝ እርሱ ነው፤ የሚወደኝም አባቴን ይወደዋል፤ እኔም እወደዋለሁ፤ ራሴንም እገልጥለታለሁ» እንዳለ፡፡ ከጥቅሱ እንደምንረዳው ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር የሚገለጠው በሁለት ነገሮች ነው፡፡ አንደኛ ትእዛዙን በመያዛችን (በማወቅና በልብ በመያዝ) ሁለተኛ የያዝነውን ትእዛዝ በመጠበቃችን ነው፡፡

ትእዛዙን የያዘና የጠበቀ ሰው እግዚአብሔርን የሚወድ ነው፡፡ እግዚአብሔርን ለሚወድ ደግሞ እግዚአብሔር ራሱን ይገልጥለታል፡፡ ራስን መግለጥ ምን እንደሆነ ሲጠይቅ «የአስቆሮቱ ያይደለ ይሁዳም ጌታ ሆይ ለዓለም ያይደለ ለእኛ ራስህን ትገልጥ ዘንድ ያለህ እንዴት ነው?» አለው፡፡ ሐዋርያው ለጠየቀው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመልስ ፡- **«የሚወደኝ ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል፤ ወደ እርሱም መጥተን በርሱ ዘንድ ማደሪያ እናደርጋለን» አለው፡፡** (ዮሐ.፲፬፥፳፩-፳፫) ወደ እርሱ መጥተን ማደሪያ እናደርጋለን ሲል ሥላሴ የሌሉበት ዓለም ኖሮ ከቦታ ወደ ቦታ እንመጣለን ማለታቸው ሳይሆን ያልተዋሐድነው የነበረውን በጸጋ እንዋሐደዋለን (ማደሪችን ያልነበረውን እናድርበታለን)፤ ያልቀረብነው የነበረውን እንቀርበዋለን ማለታቸው ነው፡፡

ፍቅር የሕግ ማሰሪያ ነውና ፍቅርን የያዘ ሁሉ ሕግን ጠባቂ ነው፡፡ እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ይኖራል፡፡ **«ትእዛዙን የሚጠብቅ በእርሱ ይኖራል፤ እርሱም በእርሱ ያድራል፡፡ በዚህም ከእኛ እንደሚኖር ከሰጠን ከመንፈሱ እናውቃለን» ተብሎ እንደተጻፈ፡፡** (**፩ኛ ዮሐ.፫፥፳፬**) ስለዚህ ሁላችንም የሥላሴ ማደሪዎች እንሆን ዘንድ ፍቅረ እግዚአብሔርን መያዝ ይገባናል፡፡ በዚህ ወቅት አንዳንዶች በዘረኝነትና በክፉ የፖለቲካ አስተሳሰብ ተለክፈው ከፍቅር ይልቅ ጥላቻን፣ ከሰላም ልቅ ጠብን፣ ከአንድነት ይልቅ መለያየትን፣ ከመተባበር ይልቅ ግለኝነትን እየሰበኩ ቤተ ክርስቲያንን እየፈተኗት ነው፡፡

ከእንዲህ ዓይነቱ ሰይጣናዊ መንገድ በመራቅ፣ ወንድሜ ወንድሜ በመባባል እየኖርን መንፈሳዊ ሕይወታችንን ማነጽና ቤተ ክርስቲያናችንንም መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡ ፍቅር ባለበት በዚያ እግዚአብሔር አለ፡፡ ክርስቲያኖች የክርስቶስ የመሆናቸው ምልክቱ ፍቅራቸው ነው፡፡ **«እርስ በእርሳችሁ ብትዋደዱ የእኔ ደቀመዛሙርት እንደ ሆናችሁ በዚህ ሁሉ ያውቋችኋል» ይላል፡፡ (ዮሐ.፲፫፥፴፭)** እንዲህ ከሆነ ሕጉን እየጠበቅን ነው፤ ሕጉንም ከጠበቅንም ወደ እግዚአብሔር የምንቀርበብትን እውነተኛውን መንገድ ይዘናል ማለት ነው፡፡ ጥላቻና መለያየትን፣ ተንኮልንና ሸንገላን የሚዘራ ግን ከሰይጣን ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ሰው ከእግዚአብሔር ርቆ ለሰይጣን ማደሪያነት የቀረበ ነው፡፡

### ፬. በንስሓ

ለእሳት ባሕርይ ቊረት (ቅዝቃዜ)፣ ለውኃ ባሕርይ ውዕየት (ሞቃትነት) እንደማይስማማው ለእግዚአብሔር ባሕርይም ኀጢአት አይስማማውም፡፡ የሰው ልጅ በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል የተፈጠረ ስለሆነ ከኀጢአት በመራቅና የጽድቅ ሥራን በመሥራት ፈጣሪውን መምሰል ይገባዋል፡፡ እግዚአብሔርን በሥራው ሁሉ ስንመስለው ርሱም ከእኛ ጋር ይሆናል፡፡ ኀጢአትን መሥራት ግን ከእግዚአብሔር ባሕርይ ጋር ስለማይስማማ ኀጢአትን በሠራን ጊዜ በረድኤቱ ይለየናል፡፡ አባታችን አዳምና እናታችን ሔዋን በገነት ሲኖሩ ብርሃን ተጎናጽፈው ይኖሩ ነበር፡፡ ብርሃኑ ስለሚሠውራቸውም አይተፋፈሩም ነበር፡፡ ሕጉን ካፈረሱ በኋላ ግን ብርሃኑ ተለያቸው፤ ዕራቆታቸውን ሆኑ፡፡ (ዘፍ.፪፥፳፱) ይህ የሚያስረዳን እግዚአብሔር በኀጢአት ምክንያት ከሰዎች እንደሚርቅ ነው፡፡ ስለዚህ ንስሐ በመግባትና ምሕረቱን በመጠየቅ ኀጢአታችንን ማስወገድና ወደ አምላካችን መቅረብ ያስፈልገናል፡፡ እኛ ከኀጢአት፣ ከበደል በንስሓ ተመልሰን ወደ እርሱ የምንቀርብ ከሆነ ርሱም ወደ እኛ ይቀርባል፤ በምሕረት ዓይኑም ይመለከተናል፡፡ «ኑ! ወደ አምላካችን ወደ እግዚአብሔር እንመለስ፤ እርሱ ሰብሮናልና እርሱም ይፈውሰናልና፤ እርሱ መትቶናልና እርሱም ይጠግነናል» ተብሎ እንደ ተጻፈ፡፡ (ሆሴ.፮፥፪)

በመጽሐፈ ፊልክስዩስ ላይ ታሪኩ የተጻፈ አንድ መነኵሴ (አረጋዊ/ ባሕታዊ) ነበር፡፡ ሰይጣን ጾር አስነሥቶበት የአንድ የጣዖት ካህን ልጅ ወደደ፡፡ ሄዶም ልጅህን አገባት ዘንድ ስጠኝ አለው፡፡ ያም የጣዖት ካህን ቆይ አምላኬን ልጠይቅ ብሎ ከጣዖት ቤት ገብቶ ቢጠይቅ ሰይጣን በጣዖቱ ላይ አድሮ ሃይማኖትህን ካድ፣ ቆብህን ቅደድ በለው አለው፤ እርሱም ሄዶ ሰይጣን የነገረውን ለመነኵሴው ነገረው፡፡ መነኵሴውም ሃይማኖቱን ክዶ፤ ቆቡን ቀድዶ በል ሃይማኖቴን ከጃለሁ፤ ቆቤን ቀድጃለሁና ልጅህን ስጠኝ አለው፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ ከቤተ ጣዖቱ ገብቶ ቢጠይቅ ፈጣሪው ፈጽሞ ስላልተለየው አትስጠው አለው፡፡ መነኵሴው እንዳልሰጠው ባየ ጊዜ ልጅህን አገኛለሁ ብየ ነው እንጅ ሃይማኖቴን የካድሁ፣ ቆቤን የቀደድሁ ለዚህ ነውን? ብሎ ንስሓ ቢገባ በሦስተኛው ሱባዔ (በሃያ አንደኛው ቀን) በአምሳለ ርግብ ተለይቶት የሄደው መንፈስ ቅዱስ ተመልሶ ሲያድርበት ታይቷል፡፡ (ተስእሎ ፬ ተስእሎ ፺፰) ይህም እግዚአብሔር በኀጢአታችን ምክንያት ቢለየንም ንስሓ ከገባን ግን ይቅር ብሎ ከእኛ ጋር እንደሚሆን፣ ወደ እርሱ እንደሚያቀርበንና የቀደመውን ጸጋችንንም እንደሚመልስልን ነው፡፡

## ፰. በቅዱስ ቊርባን

ቅዱስ ቊርባን ከእግዚአብሔር ጋር አንድ የምንሆንበት ምሥጢር ነው፡፡ ቅዱስ ቊርባን ስንቀበል አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በጸጋ ያድሩብናል፡፡ መድኅን ክርስቶስ ይህንን አስመልክቶ ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል፤ እኔም በእርሱ እኖራለሁ ብሎ እንዳስተማረ፡፡ (ዮሐ.፮፥፶፮56) በእኔ ይኖራል ሲል በጸጋ ተዋሕዶኝ ይኖራል ማለቱ ሲሆን እኔም በእርሱ እኖራለሁ ሲልም አድሬበት እኖራለሁ ማለቱ ነው፡፡ ቅዱስ ቊርባን ክርስቲያኖች ከክርስቶስ ጋር (የሚተባበሩበት) አንድ የሚሆኑበት ምሥጢር ነው ብለናል፡፡ በክርስቶስ አንድ የሚሆኑ የምእመናን ጉባኤ ቤተ ክርስቲያን ይባላል፡፡ ቤተ ክርስቲያን አንዲት የምትባለው ምእመናን ቅዱስ ቊርባንን በመቀበል አንድ አምላክ ለሚሆን ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ማደሪያዎች በመሆናቸው ነው፡፡

ሥርዐተ ቅዳሴው አንዱን ባሕርያቸውን በአንዲት የክርስቲያኖች አንድነት በማንጸር እንዲህ ብሎ የሚያተምረን ለዚህ ነው፡-
«**ዘኅቡር ህላዌከ ዕቀብ ማኅበረነ» ባሕርይህ አንድ የሆነ ሆይ! አንድነታችንን ጠብቅ**» ወደ ያዝነው ርእሰ ጉዳይ ስንመጣ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ሃይማኖትን ማወቅና፣ ጸሎትን መያዝ፣ ሕጉን መጠበቅ፣ ንስሓ መግባት መሆኑን ከላይ ባነሣናቸው ነጥቦች ተመልክተናል፡፡ የዚህ ሁሉ መደምደሚያው ግን የጌታችንን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም መቀበል ነው፡፡ የእርሱ አካል እስከመሆን የምንደርስበት ምሥጢር ነውና፡፡ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው፤ ቤተ ክርስቲያንም የክርስቶስ አካል ናት የሚባለው በዚህ ምሥጢር ነው፡፡ (ኤፌ.፩፥ ፳፫-፳፬) ይህም የእግዚአብሔርንና የክርስቲያኖች ፍጹም የሆነ መንፈሳዊ መቀራረብን የሚያስረዳ በጥልቀት ነው፡፡ በመሆኑም ሁላችንም ከዚህ ምሥጢር በመሳተፍ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይገባናል፡፡
ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ጥቅሙ ምንድን ነው?

## ፩. ረድኤተ እግዚአብሔርን ገንዘብ ለማድረግ

መዝሙረኛው ዳዊት ባነሣነው ርእስ ላይ ወደ እርሱ ቅረቡ ካለ በኋላ ወደ እግዚአብሔር ስንቀርብ ምን ዋጋ እንደምናገኝ ሲያስረዳ ይበራላችሁማል ነው ያለን፡፡ ይህንንም ብርሃነ ረድኤቱን ይሰጣችኋል ማለት ነው ብለው አባቶቻችን ተርጕመውታል፡፡ ነቢዩ በሌላኛ የመዝሙሩ ክፍል «**እግዚአብሔር ያበርህ ሊተ ወያድኅነኒ፤ እግዚአብሔር ያበራልኛል፤ ያድነኛልም» እንዳለ፡፡ (መዝ.፳፮፥፩)** ዳግመኛም «**ሶበ አኮ እግዚአብሔር ምስሌነ ይብል እስራኤል ሶበ አኮ እግዚአብሔር ምስሌነ እንተ ጊዜ ተንሥአ ሰብእ ላዕሌነ አሐዝብ ሕያዋኒነ እምውኅጡነ በከመ አንሥኡ ቊጥዓ መዓቶሙ ላዕሌነ» እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ባይሆን እስራኤል እንዲህ ይበል፡- እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ባይኖር ሰዎች በእኛ ላይ በተነሡ ጊዜ የመዓት ቊጣቸውን በላያችን ባነሡ ጊዜ ሕያዋን ሳለን በዋጡን ነበር ብየ በተጠራጠርሁ ነበር» ብሏል፡፡ (መዝ.፻፳፫፥፩-፫)** ከዚህ የምንረዳው ወደ እርሱ ለሚቀርብ ሰው እግዚአብሔር የሚረዳ መሆኑንና ከመከራ የሚያድን መሆኑን ነው፡፡ ዛሬ በሀገራችንና በቤተ ክርስቲያናችን የተደቀነው መከራ ብዙ ነው፡፡ የምእመናንና የካህናት መገደል፣ መፈናቀል፣ የንብረት ውድመት፣ ጦርነት፣ መለያየት በዝቷል፡፡ ይህንን መከራ ደግሞ ያርቅልን ዘንድ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይገባናል፡፡ እርሱ አምባ መጠጊያችን ነውና፡፡ እየሠራን መከራውን እንዲያርቅልን በንጹሕ ልብ ሆነን እንጸልይ፡፡ እኛ ሳንሠራና የድርሻችንን ሳንወጣ እግዚአብሔር በተኣምር ሁሉን ነገር እንዲያስተካክልልን መጠበቅ ግን የለብንም፡፡ ወደ እርሱ ከቀረብን እርሱ ከእኛ ጋር ይሆናል፤ እርሱ ከእኛ ጋር ከሆነም እየሠራን ችግራችንን መፍታት እንችላለን፡፡

## ፱. መልካም ሥራን ለመሥራት ይረዳናል፡፡

ወደ ርሱ ቅረቡ ያበራላችሁማል ሲል ከላይ ያየነው እንዳለ ሆኖ ሕጉን ከጠበቃችሁ፣ እርሱን ካመለካችሁ ምግባር፣ ትሩፋት ትሠሩ ዘንድ ይረዳችኋል ሲለን እንደ ሆነም ሊቃውንት ተርጕመውታል፡፡ ምግባርን ብርሃን ይለዋልና፡፡ በብርሃኖሙ ለቅዱሳን በቅዱሳን ብርሃን ... (መዝ.፺፱፥፩) ያለውን የመዝሙረ ዳዊት ንባብ ሊቁ አባ ጊዮርጊ ዘጋስጫ <<**ዝኒ ሥነ ብርሃን ዘዕሴተ ጻድቃን እስመ ምግባሩ ለሰብእ ያበርህ ሎቱ**>> **ይህ የብርሃን ጸጋ የጻድቃን ዋጋ ነው፤ ለሰው ምግባሩ ያበራለታልና ብሎ እንደ ተረጐመው፡፡(መጽሐፈ ምሥጢር ፩፥፵፫)** ያለ ረድኤተ እግዚአብሔር አነብ፣ እጽፍ፣ እደጉስ፣ እማር፣ አስተምር አርስ፣ እቆፍር ቢሉ አይሆንምና፤ ፍቅር፣ ትዕግሥት፣ የውሃት፣ ቸርነት፣ ምጽዋት የመሳሰሉትን መንፈሳውያን ምግባራትም ማከናወን አንችልምና፡፡ **«በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ የምኖር ብዙ ፍሬ የሚያፈራ እርሱ ነው፡፡ ያለ እኔ ምንም ማድረግ አይችልም። በእኔ የማይኖር ቢኖር እንደ ደረቅ ቅርንጫፍ ወደ ውጭ ይጥሉታል፡፡ ሰብስበውም በእሳት ያቃጥሉታል፡፡ በእኔም ብትኖሩ ቃሌም በእናንተ ቢኖር የምትሹትን ሁሉ ትለምናላችሁ ይደረግላችሁም እንዳለ አምላካችን፡፡»** (ዮሐ.፲፭፥፮-፯)
ከዚህ የምንረዳው ያለ እግዚአብሔር ርዳታ የመልካም ምግባር ፍሬ ማፍራት የማንችል መሆናችንን ነው፡፡ ስለዚህ ወደ እግዚአብሔር መቅረባችን በጎ ምግባር ለመሥራት ይረዳናል፡፡ በምንሠራው በጎ ምግባር ደግሞ የበለጠ ወደ እርሱ እንቀርባለን፡፡

## ፲. ከሰይጣን ፈተና ለመዳን

በዚህች ዓለም ላይ ስንኖር በተለያዩ ነገሮች እንፈተናለን፡፡ ከሁሉም በላይ ሰይጣን ከእግዚአብሔር ርቀን የዘለዓለም ሞት እንሞት ዘንድ አጥብቆ ይፈትነናል፡፡ ስለዚህ ከላይ በዘረዘርናቸው ወደ እግዚአብሔር የመቅረቢያ መንገዶችን በመያዝ (ገንዘብ በማድረግ) ወደ እርሱ ከቀረብን ከሰይጣን ፈተና እንወድቅ ዘንድ አምላካችን አይተወንም፡፡ **«አሆ በልዎ ለእግዚአብሔር ወእንብየ በልዎ ለጋኔን ወይጐይይ እምኔክሙ ቅረብዎ ለእግዚአብሔር ወይቀርበክሙ» እንግዲህ እግዚአብሔርን እሺ በሉት፤ ሰይጣንን ግን እንቢ በሉት፤ ከእናንተም ይሸሻል፡፡ እግዚአብሔርን ቅረቡት፤ ይቀርባችሁማል። እንዳለ ሐዋርያው፡፡** (ያዕ.፬፥፯-፰) ስለዚህ ከሰይጣን ፈተና ለመዳን ሰይጣንን እንቢ ማለት፣ አለመታዘዝ፣ ፈቃዱን አለመፈጸም ይገባል፡፡ በአንጻሩ ይህንን ለእግዚአብሔር ካደረግነው ወደ እኛ ይቀርባል፤ ጠላታችን ሰይጣንም ከእኛ ይርቃል፡፡ እግዚአብሔር ስንቀርበው፣ እሺ ስንለው (ስንታዘዘው) የሚቀርበን ከእኛ ለእርሱ አንዳች የሚጠቅም ዋጋ ለማግኘት አይደለም፤ ነጻ ፈቃዳችንን ለማክበር ነው እንጂ፡፡ ርሱ ሳንፈቅድለት ወደ እኛ አይመጣም፤ አያስገድድምና፡፡ ወደን ፈቅደን በመታዘዝ ከቀረብነው ግን ይቀርበናል፡፡ ስለዚህ ጠላታችን ሰይጣን ከእኛ ይርቃል፡፡

## ፬. መንፈሳዊ በረከትንና ዘለዓለማዊ ሕይወትን ለማግኘት

ወደ እርሱ የመቅረብ ትልቁ ጥቅም ግን መንፈሳዊ በረከትን ለማግኘትና የእግዚአብሔርን መንግሥት ወርሶ ለዘለዓለም ከእርሱ ጋር ለመኖር ነው፡፡ በሃይማኖት ጸንተን፣ በምግባር፣ በትሩፋት ታንፀን፣ ሕጉንና ትእዛዙን ጠብቀን፣ ኀጢአታችንን በንስሓ አንጽተን፣ የጌታችንን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ተቀብለን ከጠበቅነው አምላካችን በሚመጣ ጊዜ በዚህ አብረነው እንደ ኖርን ለዘለዓለም አብረነው እንኖር ዘንድ ወደ እርሱ ይወስደናል፡፡ (ዮሐ.፲፫፥፫) ይህን ሳናደርግ ብንጠብቀው ግን **«ሑሩ እምኔየ፤ ከእኔ ወግዱ»** ብሎ ይፈርድብናል፡፡ ወደ እርሱ ሊወስደን ይመጣል ስንል ርሱ እንደ ፍጡር በቦታ ተወስኖ የሚኖር ሆኖ አይደለም፡፡ አንደኛ እኛ በምንኖርባት በመንግሥተ ሰማያት በምልአት ሲኖር ሁለተኛ በጸጋ ተዋሕዶን (አድሮብን) ስለሚኖር ነው እንጂ፡፡ ስለዚህም ከላይ ወደ እግዚአብሔር እንዴት እንቅረብ? በሚለው ርእስ ሥር የተዘረዘሩትን ነጥቦች በመያዝ ወደ አምላካችን መቅረብ ይጠበቅብናል፡፡ እንዲህ ከሆነ በሥጋም በነፍስም ዋጋችንን እናገኛለን፡፡ ይህም ዋጋ በእግዚአብሔር ቸርነትና ይቅርታ ከእርሱ የሚሰጠን ነው እንጂ በጉልበት ቀምተን፣ በዕውቀታችን ተመራምረን የምናገኘው አይደለም፡፡ የእግዚአብሔር ቸርነቱ ለዘለዓለም አይለየን አሜን፡፡ **«ወደ እርሱ ቅረቡ፤ ያበራላችሁማል፡፡»** (መዝ.፴፫፥፭)

# 3. ኪነ ጥበብ

ጾም

በዕይነ ሕሊናችን ቀራንዮን ካላየን
ግርፋት ስቃዩን ችንካሩን ካላሰብን
መውደቅ መነሣቱን ከቶ ሳናስተውል
ብንጾም ኣይረባንም ዳግሞም
ብናከፍል።

በኪዳተ ሕሊናችን ካልሄድን ጎልጎታ
ካልተገነዘብን የተከፈለልንን ውለታ
መጾም ምን ያደርጋል ከውኃ
ከምግብ
ተጉዘን ካልደረስን ከጌታችን ወዳብ።

እጃችንን ለምጽዋት ፍጹም ሳንዘረጋ
ሥጋን ብቻ ማስራብ ኣይኖረውም
ዋጋ።

በቅዱሱ ተራራ ሲነገረን ቃሉ
ሲያስተምሩ መምህር ንስሓ ግቡ እያሉ
ሰምተን ከልተገበርን ካልኖርነው
በሕይወት
ዋጋ የለውም ጾም ምግብ
ኣለመብላት።

ከምግበ ሥጋ ኣጥብቆ ተክልክሎ
ሰዎችን ማማት በቃላት ገድሎ
እየጾሙ ኣለመጾም እየዘሩ
ኣለማፍራት
ምንኛ ድካም ነው ምንኛ ከንቱነት።

>>

>>

ማለዳ ለኪዳን ሲመሽ ለጸሎተ ሠርክ
በመቅደሱ ተገኝተን በፊቱ ብንንበረከክ
ከምሕረቱ ኣዳባባይ በቅዱሱ ሥፍራ
ም ሥጢር እያራቀቅን ቃሉን ብንዘራ
በጾምና ጸሎት እኛ ካልተቃኘን
በበጎ ምግባር በእውነት ካልተባበርን
ፍሬ ሳናፈራ መሬት ስለተጎሳቆልን
በምሳር ተቆርጠን ከእቶን እንጣላለን።

ግን፡ ጾም ጸሎታችን፡-
ዳርሶ እንዲያንኳኳ ከሰማዩ ዳጃፍ
ከሰማያዊያን ኅብረት ኣብረን
እንድንሰለፍ
በዋዛ ፈዛዛ ያሳለፍነውን ዘመን
ዘልማዳዊ ኣምልኮን ቆርጠን
ኣውጥተን
ሕዋሶቻችንን በኣንድ ኣስተባብረን
ለፈቃዱ እንገዛ ከዛሬ ጀምረን
ፈቃዱን እንፈጽም ከኣሁን ጀምረን።

ስብሐት ለእግዚኣብሔር
ወለወላዲቱ ድንግል

# 4. ግብረ ማኅበረ ቅዱሳን

“እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤” (ማቴ. ፳፰፥፲፱-፳)

## 1) አጠቃላይ ነበራዊ ሁኔታዎች

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊትና ታሪካዊት ናት፡፡ መሠረተ ሃይማኖቷና አስተምህሮዋ ከአማናዊው መምህር ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተገኘ በመሆኑ አማናዊትና ርትዕት ናት፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን «ወርቃማ» ዘመናትን ያሳለፈች ስትሆን በዚያው መጠን እጅግ ፈታኝ የሆኑ የመከራ ዘመናትንም አሳልፋለች፡፡ እነዚህም ወቅቶች ኢትዮጵያውያን አሕዛባዊ ጠባይን የተላበሰ የአኗኗር ዘይቤ እንዲከተሉ ከማድረጉም በተጨማሪ የተለያዩ እምነቶች ወደ ሀገራችን እንዲገቡ መንገድን አመቻችተዋል፡፡

ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «አባቴ እንደላከኝ እናንተንም እልካችኋለሁ» እንዲሁም «ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው» ሲል በአምላካዊ ቃሉ ያዘዘውን መሠረት አድርጋ የቅዱሳን ሐዋርያትን ፈለግ በመከተል ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን መምህራንን እያሠለጠነች በየቦታው ስታሰማራና ቅዱስ ወንጌል ስትሰብክ ስታጠምቅ የእግዚአብሔርን ልጅነት ስታሰጥ ኖራለች፤ ወደፊትም ይህንን ተልእኮዋን አጠናክራ ትቀጥላለች፡፡ (ማቴ.፳፰፥፲፱-፳፣ዮሐ.፳፥፳፩)

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የማኅበረሰባችንን ችግር ምክንያት በማድረግ የተለያዩ እምነቶች አብዛኛውን የገጠርና ጠረፋማ አካባቢ ነዋሪዎች የተሳሳተ ትምህርት በማስተማርና በጥቅም በመደለል ከቅድስት ቤተክርስቲያን ሲያርቁት ከሥላሴ ልጅነት ሲለዩት ማየት መመልከት የተለመደ እየሆነ መጥቷል፡፡ ለዚህም ለሦስት ተከታታይ ወቅቶች የተካሄዱት የሕዝብ ቆጠራ ውጤቶች ምስክሮች ናቸው፡፡

ይህ የሌሎች የእምነት ቤቶች ተጽእኖ፣ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች በቂ አለመሆን እና የምእመናን የግንዛቤ ማነስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታዮች በተካሄደው የሕዝብና ቤት ቆጠራ መሠረት ቁጥራቸው መቀነስ ማወቅ ተችሏል፡፡ በዚህም መሠረት በ፲፱፻፸፯ ዓ.ም ከመቶ ስድሳ ያህል፣ በ፲፱፻፹፯ ዓ.ም ኀምሳ በመቶኛው እና በ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ዐርባ ሦስት ከመቶ ያህል ነው፡፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲንንም በመጠባባቅ፡ «ድረሱልን፤ አስተምሩን፤ አጥምቁን፤ እኛም እንደ እናንተ ክርስቲያኖች መሆንና ክርስቲያኖች ተብለን መጠራት እንፈልጋለን» ለሚሉ ወገኖችም መድረስ አልተቻለም ነበር፡፡ ይህንንም ችግር ለመፍታት ማኅበረ ቅዱሳን በስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ አገልግሎት ከቤተ ክርስቲያን የኮበለሉትን በማስመለስ፣ አዳዲስ አማንያንን አስተምሮ በማስጠመቅና ያመኑትን በማጽናት በርካታ ሥራዎችን ሲያከናውን ኖሯል፤ አሁንም በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡

በክርስቲያናዊ ሕይወት ከሁሉም የቀደመ ተግባራችን ማመንና መጠመቅ እንደሆነ «**ያመነ የተጠመቀም ይድናል**» በማለት እግዚአብሔር አምላካችን አስተምሮናል፡፡ ሰዎችን በተለይም የቅዱስ ወንጌል ትምህርት ያልደረሳቸው ወገኖች ተምረው፣ አምነው፣ ተጠምቀው ለቅድስት ሥላሴ ልጅነት በቅተው በንስሓ ጥምቀትም ከኃጢአታቸው ነጽተው እንዲድኑ፣ ምእመናን ከአፅራረ ቤተ ክርስቲያን የቅሰጣ ሥራ ራሳቸውን ጠብቀው በምግባረ ክርስትና እንድኖሩ ማኅበረ ቅዱሳን እጅጉን ይሻል፡፡

በዚህም መሠረት ማኅበረ ቅዱሳን የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ስብከተ ወንጌል እና ሐዋርያዊ አገልግሎትን ተደራሽ የማድረግ ተግባራትን በመፈጸም ምእመናንን ማጽናት እና ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ያሉ ወገኖችን ወደ ክርስትና ለማምጣት ወይም ለመመለስ ይተጋል፡፡ በቀዳሚነት አድርጎ የተንቀሳቀሰው በጥምቀት ልጅነትን እንዲያገኙ እነርሱን የማስጠመቅ ተግባር ነው፡፡ (ማር.፲፮፥፲፮) የስብከተ ወንጌልን እና ሐዋርያዊ አገልግሎትን የማስፋፋት መርሐ ግብርን አስመልክቶ ስብከተ ወንጌል ተደራሽ ባልሆነባቸው አካባቢዎች ትምህርተ ወንጌልን በማስተማር ቅዱስ ወንጌል ያልደረሳቸውን ወገኖች እስያጠመቀ በርካቶችን ወደ ክርስትና እምነት እንድመጡ እያደረገ ይገኛል፡፡

በዚህም ሐዋርያዊ ተልእኮ ማኅበሩ በስብከተ ወንጌል አገልግሎት ተደራሽ ባለመሆናቸው ተስፋ በመቁረጥ የጠፉ ከቤተ ክርስቲያን የቀሩ ወገኖችን ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሰብስቧል፤ ጠፍተው የነበሩ እና ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ለዘመናት ተስፋ ሲያደርጉ የነበሩ ወገኖችን ተምረውና አምነው በመጠመቅ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ልጆች እንዲሆኑ አድርጓል፡፡ ስመ እግዚአብሔር የማይጠራባቸውና ስብሐተ እግዚአብሔር ያልደረሰባቸው አካባቢዎች ስመ እግዚአብሔር እንዲጠራ ስብሐተ እግዚአብሔር ተደራሽ እንዲሆን አስችሏል፡፡ ከአዳዲስ አማንያን መካከል አገልጋዮች ሰባክያነ ወንጌልን፣ ዲያቆናትንና ካህናትን አፍርቷል፡፡ ሰንበት ትምህርት ቤቶች በሌሉባቸው አካባቢዎች ሕፃናትንና ወጣቶችን እንዲመሠረቱ ከማድረጉም ባሻገር አጠናክሯል፡፡ ኦርቶዶክሳዊ ወገኖች በሌሉባቸው አካባቢዎች የሐዋርያዊ አገልግሎት ተደራሽ በመሆኑ ኦርቶዶክሳዊ ትውፊትንና ሥርዓትን አስፋፍቷል፡፡

ማኅበሩ እነዚህን መንፈሳዊ አገልግሎት ተደራሽ ከማድረጉም በላይ አዳዲስ አማንያኑ እንዲሁም ምእመኑ በሃይማኖት ጸንተው እንዲኖሩ ለማስቻል የተለያዩ መርሐ ግብራትንና ሥልጠናዎችን በማዘጋጀት ተሳትፎአቸውን እንዲጨምሩ እያደረጋቸው ይገኛል፡፡

## 2) ስብከተ ወንጌል ፈተናዎች

### 2.1 የስብከተ ወንጌል ወቅታዊ ፈተናዎች

#### 1. ውስጣዊ ችግሮች

በቤተ ክህነት መዋቅር ለስብከተ ወንጌል አገልግሎት የሚሰጠው ትኩረት አናሳ መሆን

- ዘመኑን የሚዋጅ ሰባኬ ወንጌል በብዛትም በጥራትም ማሠልጠን አለመቻል
- በብዙ ቦታዎች በየማኅበረሰቡ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን ያለመኖር
- በጠረፋማና በዓለም ወንጌልን ማድረስ አለመቻል (የሚሰጠው ትኩረት አናሳ መሆን)
- በቴክኖሎጂ የተደገፈ ስብከተ ወንጌል መፈጸም አለመቻል
- በስብከተ ወንጌል ተደራሽ ላልሆኑ እና ትኩረት ለሚፈልጉ ወገኖች ተደራሽ አለማድረግ

- ምእመናንን ሊያንጹ፣ የጠፉትን ሊመልሱ የሚችሉ ጉባኤያትን ማከናወን አለመቻል
- የቤተ ክርስቲያንና አገልጋዮች ጥምረትና ስምሪት የተማጣጠነ አለመሆን
- የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ በአግባቡ የተደራጀ እና የተዋቀረ አለመሆን
- እቅድ መር ሥራ መሥራት አለመቻል
- ዘመኑን የዋጁ ካህናትን በብዛትና በጥራት አለማሠልጠን
- የክህነት አመራረጥ፣ አሰጣጥና መረጃ አለመኖር
- ሥልጠናና ክትትል አለማድረግ
- ዘመኑን የሚመጥን አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ካህናትን አለማሠልጠን
- በብዙ ቦታ ካህናት አለመኖር ምክንያት ቁጥራቸው የማይታወቅ በርካታ አብያተ ክርስቲያናት መዘጋት
- ወጥነት ባለው ሥርዓተ ትምህርት ምእመናንን አለማስተማር
- ምእመናን ዕውቀት እንዲኖራቸው የሚያስችል ትምህርት መስጠት አለመቻል
- ለወጣቶች እና ለሕጻናት መንፈሳዊ ሕይወት በቂ ክትትል አለመኖር
- በሁሉም ቦታዎች የተጠናከረ ሰንበት ት/ቤት አለመኖር

**2. ውጫዊ የስብከተ ወንጌል ፈተናዎች**

የአፅራረ ቤተ ክርስቲያን ተጽዕኖ

- ከማኅበራዊ ሕይወት በማግለል በግድ ወደ እምነታቸው መውሰድ
- የመጥላትና የማግለል
- በሥራ በኀዘንና በደስታ እንዳይሳተፉ ማድረግ
- በኃይል እምነታቸውን ማስፋፋት
- ቤተ ክርስቲያንን በማቃጠል
- ካህናትን እና ምእመናንን በአሰቃቂ ሁኔታ መግደል፣ ማፈናቀል፣ ሀብት ንብረታቸውን መዝረፍ
- ንዋያተ ቅድሳትን መዝረፍ
- በርዳታና በማኅበራዊ ተቋማት ሰበብ የሐሰት ትምህርታቸውን ማስፋፋት
- ምእመናንን በገንዘብ በመርዳት ምግብ፣ አልባሳት እና ሌሎች ድጋፎችን በማድረግ ሽፋን የሐሰት ትምህርታቸውን ማስፋፋት
- ወደ ውጭ ሀገራት ለሥራና ለትምህርት በመላክ በጥቅም የመሳብና ወደራሳቸው የመውሰድ ሥራ መሥራት
- የምእመናንን ልጆች በነፃ በማስተማር የቅሰጣ ሥራ መሥራት

- ነፃ የጤና አገልግሎት በመስጠት
- የጤና፣ የትምህርት፣ የልማት ሥራዎችን በመሥራት መሰልተቋማትን በማስፋፋት
- ፖለቲካዊ እንቅስቃሴን በመጠቀም እምነታቸውን ማስፋፋት
- ቤተ ክርስቲያንን በሐሰት ትምህርት በጨቋኝነት በብሔር ፣በኢኮኖሚ፣ በፍትሕ መውቀስ
- ጥንታዊ የቤተ ክርስቲያን ቦታዎችን እየመረጡ ይዞታን በመንጠቅ
- ምእመናንን በማሸማቀቅ ወደ ራሳቸው እምነት መውሰድ
- ለእምነታቸው መስፋፋት በትኩረት በመሥራት የቅሰጣ ሥራቸውን በማስፋፋት
- የሐሰት መምህራንን በማብዛት እና በማሰማራት
- ትልልቅ ኮንፈረንሶችን በተለያዩ ቦታዎች በማከናወን
- የሚሽነሪ ማእከላትን በማስፋፋት
- የውጭ ሀገር ዜጎችን በማሰማራት
- የተለያዩ መጻሕፍትን፣የድምፅ ወምስል ውጤቶችን በብዛት በማሰራጨት
- ቅዱሳት መጻሕፍትን በመቀሰጥ
- ምትሐታዊ ፈውስን በማስፋፋት ለሐዋርያዊ የቤተክርስቲያን አገልግሎት እንቅፋት በመሆን ይገኛሉ፡፡

## 3) የማኅበረ ቅዱሳን የስብከተ ወንጌል እና ሐዋርያዊ አገልግሎት

### 3.1 ማኅበረ ቅዱሳን በስብከተ ወንጌል እና ሐዋርያዊ አገልግሎት ተልእኮ

በቅዱስ ወንጌል የተጠቀሰውን ትልቁን አምላካዊ ትእዛዝ ለመፈጸም የሚያስችሉ ስብከተ ወንጌል እና ሐዋርያዊ አገልግሎት ጥናቶችን በማካሄድና ችግር ፈቺ ስልቶችን በማዘጋጀት፣ ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ተልእኮ በመፈጸም በማስተማር ምእመናንን ማጽናት ፣ቅዱስ ወንጌል ያልደረሳቸውን ወገኖች በማስተማር ያመኑትን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም የማስጠመቅ፤ የማጽናት እና ምእመናንን ከአፅራረ ቤተ ክርስቲያን ቅሰጣ የመጠበቅ ሥራዎችን ይሠራል፡፡ በዚህም መሠረት ብዙዎችን በሃይማኖት ጽኑዓን በምግባር ርቱዓን የሆኑ የቤተ ክርስቲያን ልጆችን በማፍራት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የሚገቡ ምእመናንን የማብዛት ሥራ እየሠራ ይገኛል፡፡ (ማቴ ፳፰፥፲፱፡ማር ፲፮፥፲5፡ዮሐ ፳፥፳፩፡፳፩፥፲፮፡ የሐዋ፡፡ሥራ 2፥42-47፡ገላ 5፥12)

ይህንን ሐዋርያዊ አገልግሎት በተጨባጭ ባልተደረሰባቸው አካባቢዎች ለማድረስ በሚከተሉት ዋና ክፍላት ተደራጅቶ ከታች የተዘረዘሩትን የስብከተ ወንጌል እና ሐዋርያዊ አገልግሎቶችን ለበርካታ ዓመታት ሲያከናውን ኖሯል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ በ2015 እና 2016 ዓ.ም ያከናወናቸውን ሐዋርያዊ አገልግሎቶች ብቻ ለይተን እንመልከት፡፡

### 3.2 የማኅበረ ቅዱሳን ስብከተ ወንጌል እና ሐዋርያዊ አገልግሎት ከ2015 ዓ.ም እስከ 2016 ዓ.ም

1.ክብረ ክህነትን ለማስጠበቅ እና ካህናት የኖላዊነት ተግባርን እንዲያከናውኑ ለማገዝ

❖ ለ3641 ካህናት በክብረ ክህነት እና ኖላዊነት (መምህረ ንስሓነት) ሥልጠና በመሥጠት ለአገልግሎት እንዲሰማሩ አድርጓል፡፡

2.በልዩ ልዩ ቋንቋዎች በስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ ለሚሰማሩ

❖ 3216 ሰባክያነ ወንጌል፣

❖ በሐዋርያዊ አገልግሎት ልዩ ተልእኮ ተሰጥቷቸው የሚያስተባብሩ እና ፈርቀዳጅ የሚሆኑ 1059 የጎሳ መሪዎች እና ሌሎች አስተባባሪ አካላት ሥልጠና በመሥጠት ለአገልግሎት አሰማርቷል፡፡

3.በስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ አገልግሎት ለሚሰማሩ 213 አገልጋዮች ወርኃዊ ድጎማ በማድረግ እና ደሞዝ በመክፈል ለሐዋርያዊ አገልግሎት እንዲሰማሩ አድርጓል፡፡

❖ በእነዚህም መምህራን 22,824 ጉባኤያትን በልዩ ልዩ ቦታዎች እና ሁኔታዎች ተከናውነዋል፡፡

4. የስብከተ ወንጌል አገልግሎትን ተደራሽ በማድረግ ምእመናንን ለማጽናት፣የጠፉ ወገኖችን ለመመለስና አዳዲስ አማንያንን ለማስጠመቅ የሚያግዙ

❖ በልዩ ልዩ ቋንቋዎች 430 ትምህርታዊ ጉባኤያት በተለያዩ አካባቢዎች ተካሂደዋል፡፡

5. ስብከተ ወንጌል አገልግሎትን በልዩ ልዩ ቋንቋዎች ተደራሽ ለማድረግ

❖ የ135 ሰዓት ርዝማኔ ያላቸው በአሥራ ሁለት ቋንቋዎች በቤንችኛ፣ በካፊ ኖኖ፣ በሜኤኒትኛ፣ በጋሞኛ፣ በኮንሶኛ፣ በአሌኛ፣ በወላይትኛ፣ በጌዲዮፋ፣ በሲዳምኛ፣ በማሌኛ፣ በአራፍ እና ከምባትኛ ቋንቋዎች የድምጽ ወምስል የነገረ ሃይማኖት ትምህርት ዝግጅትና ሥርጭት ተደርጓል፣

❖ በሁለት ቋንቋዎች ወላይትኛ እና ጋሞኛ ቋንቋዎች የዓምደ ሃይማኖት መጽሐፍ ትርጉም፣

❖ በሁለት ቋንቋዎች ወላይትኛ እና ጋሞኛ የውዳሴ ማርያም ጸሎት መጽሐፍ ትርጉም፣

❖ በ10 ቋንቋዎች የነገረ ድኅነት ትምህርት ትርጉም ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡

❖ በ13 ቋንቋዎችም (በአሪኛ፣ ማሌኛ፣ ጋሞኛ፣ ኮንሶኛ፣ ወላይትኛ፣ ዳውሮኛ፣ሐዲይሳ፣ ጌዲዮፋ፣ ሲዳምኛ፣ ከፍኛ፣ ቤንችኛ፣ ኦሮምኛ፣ ከምባትኛ፣ ትግርኛ፣) ትምህርቶችን በማዘጋጀት፣ በመተርጎምና የአርትዖት ሥራ በመሥራት ለሚሳተፉ 32 አገልጋዮች ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

❖ የኤዲቶርያል (አርትዖት) ውክልናም ለ13 ቋንቋዎች ተሰጥቷል፡፡

6. የጠፉትን ለመመለስና ቅዱስ ወንጌል ያልደረሳቸውን ወገኖች አስተምሮ ለማስጠመቅ በተለያዩ አካባቢዎች ተደራሽ በተደረገው ሐዋርያዊ ተልእኮን የማስፋፋት ተግባር

- 91 415 አዳዲስ አማንያን በሀገር ቤት
- 172 አዳዲስ አማንያን ደግሞ በውጭ ሀገራት

ተምረው አምነው በመጠመቅ የቅድስት ሥላሴ ልጅነትን በማግኘት የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን አባላት ሆነዋል፡፡

7.በካህናት እጥረት ተዘግተው ለነበሩ እና ማኅበሩ ለሐዋርያዊ ተልእኮ ማስፋፊያነት ላሠራቸው 37 አብያተ ክርስቲያናት ካህናት ተቀጥረውላቸው እንዲከፈቱ እና ለምእመናን አገልግሎት እንዲሰጡ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው፡፡

8.በተለያዩ አህጉረ ስብከት ለአዳዲስ አማንያን መገልገያ የሚሆኑ

- አሥራ ዘጠኝ ሕንጻ አብያተ ክርስቲያናት እና
- አሥራ ሰባት መካነ ስብከት አደራሾች በመሠራት አገልግሎት እንድሰጡ ተደርጓል ፡፡

9.ስብከተ ወንጌልን በተለያዩ መንገዶች ተደራሽ ለማድረግ በአማርኛ እና ኦሮምኛ ቋንቋዎች በመሠረታዊ የርቀት ትምህርት መርሐ ግብር

- 2413 ተማሪዎች በሞጁል እና 177 ተማሪዎች በኢለርኒንግ የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን መሠረተ እምነት እንዲማሩ ተደርጓል፣
- ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ 437 ተማሪዎችን ማስመረቅ ተችሏል፡፡
- በትግርኛ ቋንቋም ለማስጀመር የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ተጠናቀዋል፡፡

10. ልዩ ትኩረት ለሚፈልጉ ወገኖች ማለትም

- ለዓይነ ሥውራን በሰባት ማእከላት ትምህርታዊ ጉባኤያት፣ የውዳሴ ማርያም እና ሰኔ ጎልጎታ የጸሎት መጽሐፍ በብሬል ኅትመት እና ሥርጭት ፣አሥር የድምጽ መጻሕፍት በማዘጋጀት እንድሠራጩ የተደረገ ሲሆን
- ለሕግ ታራሚዎችም በ25 ማረሚያ ቤቶች ስብከተ ወንጌልን ተደራሽ የማድረግ ተግባር በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

11. በውጭ ሀገር በተለይም በመካከለኛው ምሥራቅ፣ አቡዳቢ፣ ሩቅ ምሥራቅ፣ አውስትራሊያ ፣ደቡባዊ አፍሪካ እና አውሮፓ ለሚፈጸመው የስብከተ ወንጌል አገልግሎት ድጋፍና የመምህራን ምደባ በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡

12. የስብከተ ወንጌል አገልግሎትን በኅትመት ተደራሽ በማድረግ ምእመናንን ለማጽናት እና የጠፉትን ለመመለስ የሚያግዙ

- የክብረ ክህነት እና ነገረ ክርስቶስ መጻሕፍት ታትመው ለስርጭት እንድበቁ ተደርጓል፡፡

13. የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ስብከተ ወንጌል እና ሐዋርያዊ አገልግሎት በተመለከተ በማኅበረ ቅዱሳን የቴሌቪዥን “ግብረ ሐዋርያት” ዓምድ በማዘጋጀት በማስተላለፍ ላይ ይገኛል፡፡

### 3.3 በአገልግሎቱ የተገኙ ውጤቶች

- የተበተኑ ምእመናን መሰባሰብ፣ የጠፉትን መመለስ
- ቅዱስ ወንጌል ያልደረሳቸው ተምረው አምነው መጠመቅ እና የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ልጆች መሆን
- ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ኩላዊት መሆኗን ማስመስከር
- ዱስ ወንጌል ሲሰበክ የሰሙ ብዙዎች የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ድምፅ መናፈቅ
- ክርስቲያናዊ ትውፊትና የአብያተ ክርስቲያናት መስፋፋት ፣ ስመ እግዚአብሔር መጠራት ስብሐተ እግዚአብሔር መድረስ
- የመናፍቃን አዳራሽ፣ የጣዖት ቤቶች መዘጋት፣የሌላ ቤተ እምነት መሪዎች ወደ ቅድስት ቤተክርስቲያን መምጣት
- በአንዳንድ አካባቢ ያሉ ሰዎች ከአረማዊ ጠባይ ወደ ክርስቲያናዊ ጠባይ መሸጋገር
- የሰንበት ት/ቤቶች መመሥረት መጠናከር፣ ከአዳዲስ አማንያን መካከል የአገልጋዮች መገኘት (መዘምራን፣ ሰባክያን፣ ዲያቆናት፣ ካህናት)

### 3.4 በአገልግሎቱ ያጋጠሙ ተግዳሮቶች

- በአገልግሎቱ ዙሪያ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች በቂ መልስ መስጠት አለመቻል
- የአብያተ ክርስቲያናት መዘጋት
- ሰንበት ት/ቤቶች አለመኖር፣ አለመደራጀት፣ ተገቢውን አገልግሎት መስጠት አለመቻል
- የአፅራረ ቤተ ክርስቲያን ወረራ
- የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ከሚጠበቀው በታች መሆን
- የቤተ ክህነት መዋቅር ለስብከተ ወንጌል አገልግሎት የሚሰጠው ምላሽ በእጅጉ ውሱንነት ያለበት መሆን
- በተደጋጋሚ በመከሠት ላይ ያለው አካባቢያዊ የፀጥታ ችግር
- በሁሉም ቦታ አገልግሎቱን ለማስፋፋት የበጀት እጥረት መኖር

### 3.5 የማኅበረ ቅዱሳን 2017 ዓ.ም የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ አገልግሎቶች የትኩረት አቅጣጫዎች

- ስብከተ ወንጌልን በመሠረታዊ የርቀት ትምህርት መርሐ ግብር በአማርኛ፣ በኦሮምኛ እና ትግርኛ ቋንቋዎች በሞጁል እና ኢንተርኔት ትምህርት ተደራሽ በማድረግ 2000 ሰዎችን ማስተማርና እና 1000 ተማሪዎችን ማስመረቅ
- የስልክ የስብከተ ወንጌል (call center telephone evangelism) አገልግሎት በ ሦስት ልዩ ቋንቋዎች በሳምንት ለ አምስት ቀናት አገልግሎት መስጠት

◈ አምስት የማኅበራዊ ሚዲያዎችን በመጠቀም በአራት ልዩ ልዩ ቋንቋዎች በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ዶግማ፣ ሥርዓትና ትውፊት ላይ ያተኮሩ እና ምእመናንን ሊያንጹ የሚችሉ ትምህርቶችን ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜ በማዘጋጀት ተደራሽ ማድረግ

◈ ስብከተ ወንጌልን በኅትመት ሚዲያ ተደራሽ ለማድረግ በ10 ቋንቋዎች (2 የተለያየ ይዘት ያላቸው ቡክሌቶች፣ የጸሎት መጻሕፍ በሁለት ቋንቋዎች እና መጻሕፍ በሁለት ቋንቋዎች፣ በተመረጡ አምስት የሀገር ውስጥ ቋንቋዎች ትምህርቶችን በድምፅ ወምስል ማዘጋጀት እና ማሠራጨት

◈ ለስብከተ ወንጌል አገልግሎት ብቁ የሚሆኑ መምህራንን በደረጃ አንድ 1500 እና በደረጃ ሁለት 150 መምህራን ማሠልጠንና ማሰማራት

◈ 200 መምህራንን ለስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ አገልግሎት በድጎማ ማሰማራት፣

◈ የሐዋርያዊ አገልግሎትን ተደራሽ በማድረግ ከውጭ ሀገራት ዜጎች 1500 አዳዲስ አማንያንን ማስጠመቅና ማጽናት፣

◈ በሀገር ቤት 60 ሺህ አዳዲስ አማንያን እና 5000 የጠፉ ወገኖችን በመመለስ ሥርዓተ ጥምቀት ማስፈጸም ለዚህም 60 ትምህርታዊ ጉባኤያትን እና በ30 አካባቢዎች የመምህራን ስምሪቶችን ማከናወን፣

◈ ምእመናንን ለማጽናት ትኩረት በሚፈልጉ አካባቢዎች 20 የማጽናት ጉባኤያት እና በኩታ ገጠም ወረዳዎች አራት ሐዋርያዊ ጉዞዎችን ማከናወን፣

◈ ልዩ ፍላጎት ላላቸው እና ትኩረት ለሚፈልጉ ወገኖች ማለትም ለዓይነ ስውራን በአሥር ማእከላት ጉባኤ፣ የስብከተ ወንጌል አገልግሎት መስጠት ፣ለሕግ ታራሚዎች በ30 ማእከላት፣ በሱስ ለተጠቁና ኀዳና ተዳዳሪዎች ለሆኑ ወገኖች በ15 ማእከላት ተደራሽ ማድረግ ይገኝበታል፡፡

◈ ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ እና ማኅበረሰብን እንድፈጠር ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ ላይ ያተኮሩ 200 ትምህርታዊ ጉባኤያትን ማከናወን እና 300 አርአያና ምሳሌ የሚሆኑ ቤተሰቦችን ማዘጋጀት ይገኝበታል፡፡

### 3.6 ማጠቃለያ

ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እኔም እላካለሁ በማለት፡-

❈ በፈረሰው ቅጽር በኩል የመቆም ኃላፊነት የእያንዳንዱ ድርሻ በመሆኑ ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ አድርገን በስሑታን ትምህርት ለተወሰዱት፣ቃለ እግዚአብሔርን ናፍቀው በሜዳ ለሚቅበዘበዙት ወገኖቻችን እንደርስላቸው ዘንድ "ኑ የወንጌል ማኅበርተኞች እንሁን" እያለ ማኅበረ ቅዱሳን መንፈሳዊ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

***"መልካም ሥራን ለመሥራት አንታክት። ... ለሰው ሁሉ ይልቁንም ለሃይማኖት ቤተ ሰዎች መልካምን እናድርግ።" ገላ. ፮÷፱-፲***

ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን



## 5. ቤተ አናግድ

### የማኅበረ ቅዱሳን ድጋፍ ለቅዱሳት መካናትና ለአብነት ትምህርት ቤቶች

ሰላም ውድ አንባብያን! የዛሬ እንግዳችን ዲያቆን ደረጀ ጋረደው ይባላሉ። ዲያቆን ደረጀ በማኅበረ ቅዱሳን አስቀድሞ "ቅዱሳት መካናትና መንፈሳዊ አገልግሎቶች ማስተባበሪያ" አሁን ደግሞ "የቤተ ክርስቲያን ሁለንተናዊ እድገትና መንፈሳዊ ትምህርት ቤት አገልግሎት" በተሰኘው የአገልግሎት ክፍል የማስተባበሪያ ኃላፊ ሲሆኑ ስለማስተባበሪያውና በማስተባበሪያው በኩል ስለሚከናውኑ አገልግሎቶች በሰፊው አንሥተናል። ከእንግዳችን ጋር ያደረግነውን ቃለ መጠይቅ ክፍል አንድ ቀጥሎ እንደሚከተለው እናቀርብላችኋለን፤ ትከታተሉን ዘንድ በአክብሮት እንጋብዛለን

**መጽሔተ ተልእኮ፡-** ማኅበረ ቅዱሳን እንደ ተቋም ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ በቅዱሳት መካናትና በአብነት ትምህርት ቤቶች ላይ ምን ምን ተግባራትን አከናወነ?

**ዲያቆን ደረጀ፡-** ማኅበረ ቅዱሳን ቀደም ሲል ቅዱሳት መካናት የሚል ማስተባበሪያ በ፺ዎቹ መጀመሪያ አካባቢ በ"ሙያ አገልግሎትና ተራድኦ" ክፍል ሥር ለገጠር አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ጊዜያዊ ድጋፍ እንዲያደርግ ካዋቀረ በኋላ በጊዜው በዚህ ማስተባበሪያ በኩል ከልዩ ልዩ በጎ አድራጊዎች ምእመናን የሚሰበሰቡ የመባዕ ስጦታውችን፣ የእህል ርዳታንና የመሳሰሉትን ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ገዳማትና አድባራት በመላው ሀገራችን እየተዘዋወረ ማሠራጨት (ማከፋፈል) ጀመረ። በወቅቱ ጊዜያዊ ርዳታ ላይ ያተኩር እንጂ በኋላ በ ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ደግሞ ዐራት ባለሙያዎችን በመቅጠር በመሠረታዊ የገዳማት፣ የአብነት ትምህርት ቤቶችና የገጠር አብያተ ክስቲያናት ችግርና መፍትሔዎች ላይ ጥናት እንዲያደርጉ የባለሞያዎች አጥኚ ቡድን አዋቀረ።

በተዋቀረው ቡድንም ፳፬ ገዳማት ተመርጠው ጥናት ተደረገባቸው። የጥናቱ ዋና ዓላማም ገዳማት፣ አድባራትና የአብነት ትምህርት ቤቶች አመሠራረት፣ ቀድሞና አሁን የሚገኙበት ሁኔታ እንዲሁም ያላቸው ክብር እንዲታወቅ በመረጃ የተደገፈ ጥናት በዝርዝር ማቅረብ ነበር። ሌላው በጥናቱ መሠረት ለዘላቂ መፍትሔ የሚሆኑ ፕሮጀክቶችን በመንደፍ ችግሮቹን መፍታት የሚል ሐሳብ ነበር።

በዚህም የአብነት ትምህርት ቤት መምህራንና ተማሪዎች በአታቸውን በመልቀቅ ወደ ከተማ የሚፈልሱበትን ምክንያት ማወቅና ፍልሰቱን የሚያስቆም መፍትሔ ማበጀት ተጨማሪ የጥናቱ ዓላማ ነበር። ገዳማትና አድባራት በወቅቱ የሚገኙበትን ሁኔታና ያሉባቸውን ዋና ዋና ችግሮች በተንቀሳቃሽ ምስሎች፣ በፎቶ ግራፍና በድምጽ የተቀነባበረ መረጃ በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ አዘጋጅቶ ለድጋፍ ሰጪዎች ምእመናን ማቅረብ የሚሉ ሐሳቦችም ተካተውበታል። በጥናቱ የሚሰባሰቡ መረጃዎችን የሚሠሩ የፕሮጀክት እንቀስቃሴ ሂደቶችን ለመከታተልና ለመገምገም እንዲረዱ እንዲሁም ሌሎች ገዳማትና የአብነት ትምህርት ቤቶች ፕሮጀክቶቹን ለመሥራት ለሚፈልጉ የጥናት መረጃዎቹን በቀላሉ እንዲሰጥም ሆኖ ተዘጋጀ።

ከዚያም በኋላ ማኅበሩ እንዚህን ተግባራት በባለቤትነት እንዲመራና እንዲያስተባብር ያዋቀረው ይህ ማስተባበሪያ "ቅዱሳት መካናት" ወደ ሚለው ስያሜ ከመምጣቱ በፊት በተለይ በ፲፱፻፺፰ እና በ፲፱፻፺፱ ዓ.ም አገልግሎቱ ቅዱሳት መካናት ላይ ያተኮረ መሆኑን በመገንዘብ "የቅዱሳን መካናት ልማትና ተራድኦ" የሚል ስያሜ ተሰጥቶት የተጠኑ ፕሮጀክቶችን መተግበር ጀመረ። ከዚያም በ፳፻ ዓ.ም "ቅዱሳት መካናትና ማኅበራዊ አገልግሎት ዋና ክፍል" ተብሎ የነበር ሲሆን እንደገና "ማኅበራዊ አገልግሎት ማስተባበሪያ"ን ለይቶ በማውጣት "የቅዱሳን መካናትና አብነት ትምህርት ቤቶች ዋና ክፍል" ተብሎ ተሰየመ።

**መጽሔተ ተልእኮ፡-** ማኅበረ ቅዱሳን በቅዱሳት መካናትና የአብነት ትምህርት ቤቶች ላይ የአገልግሎት መጀመሪያ ሂደቱ ምን ይመስል ነበር?

**ዲያቆን ደረጀ፡-** የመጀመሪያዎቹ ሂደቶች በተለይ በ ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ገዳማትና አድባራት ያሉበት ደረጃ በዘላቂነት ራሳቸውን ማገዝ እንዲችሉ የጥናት መነሻ ነው ማለት ይቻላል። ከዚያ በፊት ግን ዕጣን፣ ዘቢብ፣ እና ሌሎች የንዋያተ ቅዱሳትና የገንዘብ ድጋፎች ሲደረጉ የነበሩ ቢሆንም ይህን ወደ ምእመኑ ተደራሽ ለማድረግ እና ግንዛቤ ለመፍጠር ግን ሰፊ ችግር ነበር። ከዚህም ባሻገር በቀለብ ችግር፣ በተፈጥሮ የሚድርሱ አደጋዎች የአብነት ትምህርት ቤት ተማሪዎችና፣ መምህራን፣ ገዳማውያን ባልተጠበቀ ሁኔታ ሲሰደዱ ለገዳማውያንና ለአብነት ተማሪዎች ጊዜያዊ ድጋፍ ማድረጉን አጠናክሮ ቀጠለ።

ቀደም ሲል በባለሙያዎች አጥኚ ቡድን በ ፲፱፻፺፩ ዓ.ም የተጠናውን ጥናት መነሻ ሐሳብ ፳፬ ገዳማት ላይ ብቻ ነበር ያተኮረው፤ በ፲፱፻፺፫ ዓ.ም በተደረጉ ጥናቶች ደግሞ ወደ ዘላቂ የልማት ፕሮጀክቶች እያደገ በመምጣት ከጊዜያዊ ድጋፍ ባሻገር ወደ ቋሚ የፕሮጀክት ሐሳብ አድጎ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመንደፍ መሥራት ተጀመረ።

በተጨማሪም ማኅበሩ በሁለተኛው ስልታዊ ዕቅድ በ ፳፻፬ ዓ.ም ቅዱሳት መካናትና ገዳማት ላይ ብቻ ይሠራ የነበረውን ሥራ በተደረገው በተጨማሪ ጥናት መሠረት ወደ አብነት ት/ቤቶች በማሳደግና የአገልግሎት ድርሻውን ከፍ አደረገ። ከዚህም በኋላ ከ ፳፻፬- ፳፻፰ ዓ.ም ባለው የአብነት ትምህርት ቤት ማጠናከሪያና ማቋቋሚያ መርሐ ግብር ተብሎ በማቋቋም በተለይ የአብነት ትምህርት ቤቶችን ለመርዳት "በእንተ ስማ ለማርያም" በሚል መርሐ ግብር ሰፊ እንቅስቃሴ ተደረገ።

**መጽሔተ ተልእኮ፡-** ማኅበረ ቅዱሳን ቅዱሳት መካናትና የአብነት ትምህርት ቤቶችን አስመልክቶ በዚህ ዙሪያ ያለው አገልግሎት ምን ምን ያካትታል? ይህ ጉዳይ የሚመለከተው ማስተባበሪያ አሁን ካለው አገልግሎት አንጻር ምን ያህል ግቡን መምታት ችሏል?

**ዲያቆን ደረጀ፡-** በየስልታዊ ዕቅዱ የሚቀመጡ ተግባሮች የተለያዩ ሲሆኑ ዓላማዎቹም እያደጉ መምጣት ችለዋል። መጀመሪያ አካባቢ ከላይ እንደተገለጹት ያከናውን የነበረው ጊዜያዊ ድጋፎችን ነበር። በሂደት ግን ቋሚ ፕሮጀክቶችን በመንደፍ ዘላቂ መፍትሔዎችን መገንባት ችሏል። ሁሉም ዓላማዎች ችግሮችን መቅረፍና ተገቢውን መፍትሔ በመስጠት የተለያዩ ቋሚ የልማት ፕሮጀክቶችን አጥንቶ በመቅረጽ ገዳማውያኑ ራሳቸውን እንዲችሉና እንዲያቋቁሙ የሚሉ መሠረታዊ ይዘት የነበራቸው በመሆኑ በዚያ መልኩም ማድረግ ተችሏል። በተጨማሪም ገዳማትና በነሱ ውስጥ የሚገኙ ቅዱሳት መጽሐፍትን፣ የተለያዩ ቅርሶች ባሉበት ተጠብቀው እንዲቆዩና ለትውልድ እንዲተላለፉ ማስቻል፣ የአብነት ት/ቤት ትውፊታዊ ሂደቱ እንደቀድሞው ተጠናክሮ እንዲቀጥል የአብነት ት/ቤቶችን መርዳት ሌላው የውቅቱ ዓላማው ነበር።

ይሁን እንጂ በየዘመኑ ስልታዊ እቅዱ በተቀየረ ጊዜ ዓላማውም እንደዚያው እየተሸሻለ የመጣ ሲሆን አሁን የቅዱሳት መካናትና አብነት ትምህርት ቤቶች በኢኮኖሚ እንዲሁም በልማት ላይ የሚኖረው ውጤታማነታቸው ላይም አቅዶ በመሥራት ላይ ይገኛል። በጎ አድራጊ ምእመናንን በማስተባበር የገንዘብ፣ የመጠለያ፣ የአልባሳትና የመጻሕፍት ድጋፍ ለአብነት ት/ቤቶች እንዲያደርጉ ይሠራል።

ቅዱሳት መካናትንና የአብነት ትምህርት ቤቶችን በማጠናከር ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ጉልህ አስተዋጽኦ እንዲኖራቸው ማድረግ፣ ሌሎች አሁን በቅርብ ጊዜ የተጨመሩ ደግሞ በጠረፋማ አካባቢዎችና ስብከተ ወንጌል ባልተስፋፋባቸውና የአገልጋይ እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች የአብነት ት/ቤቶችን በማስፋፋት ተተኪ ትውልድንና የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን ማፍራት፣ የተደራጀ መረጃና ወጥ የሆነ ሥርዓተ ትምህርት አዘጋጅቶ መተግበር፣ የአብነት ትምህርት ቤቶችን ሁለንተናዊ አቅም ማሳደግ፣ በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ላይ ሥልጠና መስጠት እነዚህ ሁሉ ማኅበሩ በማስተባበሪያው በኩል የሚያከናውናቸው ቋሚ ተግባራት ናቸው።

የአብነት ተማሪዎች ዘመናዊ ትምህርትን የዘመናዊ ትምህርት ተማሪዎችም የአብነት ትምህርትን እንዲያገኙ በማድረግ ዘመኑን የዋጁ አገልጋዮችን ማፍራት እንዲቻል የአባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ነጻ የትምህርት ዕድል በተመረጡ ቦታዎች ማዘጋጀት፣ ለገዳማት፣ ለአድባራትና ለአብነት ትምህርት ቤቶች በዘላቂነት ራሳቸውን እንዲችሉ መርሐ ግብራትን ማዘጋጀት፣ ገዳማትና አድባራት እንዲጠነከሩ ትኩረት አድርጎ መሥራት፣ የተመረጡ የአብነት ትምህርት ቤቶችንና አድባራትን ማእከል እንዲሆኑ መሥራት፣ ለዘላቂነት የሚሆን የገንዘብ ምንጭ የሚሆኑ ፕሮጀክቶችን ማጥናትና መተግበር፣ ገዳማት የታሪክ ትምህርትና የጠንካራ መንፈሳዊነት ማእከል እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ማኅበሩ በዚህ ማስተባበሪያ በኩል በዋናነት የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት ናቸው።

**መጽሔተ ተልእኮ፡-** የማኅበሩ አሁን ያለው አገልግሎት ከተነሣበት ዓላማ ጋር ሲታይ ምን ይመስላል?

**ዲያቆን ደረጀ፡-** ከተነሣበት ዓላማ አንጻር ሲታይ በገዳማትና በአብነት ትምህርት ቤቶች ላይ ትልቅ ለውጥ አምጥቷል። ከተሠሩት መካከልም ገዳማት እርስ በእርስ ግንኙነት እንዲኖራቸው፣ እንዲወያዩ፣ በኢኮኖሚ እንዲደራጁ፣ ራሳቸውን ችለው ማኅበረሰቡን እንዲያግዙ፣ በተለያየ ምክንያት ወላጆቻቸውን ያጡ ሕፃናትን እንዲረዱ ከማድረግ አኳያ የተለያዩ ሥራዎች ተሠርተዋል። ገዳማት ራሳቸውን ለመቻል እንዲሠሩና በልማት ራስን መቻል አንዱ ተግባራቸው እንዲሆን ያስቻለ ሲሆን በተለይ የገዳማት መነሻ የሆነችውን የግብፅ ገዳማትን እንዲጎበኙና ገዳማቱ የደረሱበትን ሁኔታ እንዲያውቁ በማድረግ መነሣሣት እንዲፈጠር ተደርጓል።

ምእመናን የአብነት ጉባኤ ትምህርት ቤቶች ለሀገርና ለቤተ ክርስቲያን ያላቸውን ጥቅም እንዲረዱና የሚጠበቅባቸውን ድርሻ እንዲወጡ ግንዛቤ መፍጠር የተቻለ ሲሆን ጉባኤ ቤቶችም ተተኪ መምህራንና አገልጋዮችን እንዲያፈሩ ትልቅ ሥራ ተሠርቷል። ብዙ ዓመታት ወንበር ተክለው ሲያስተምሩ አስተዋሽ ያልነበራቸው ተስፋ ወደ መቁረጥ ደርሰው የነበሩ መምህራንን በትንሹ በመደገፍ ተስፋቸው ለምልሞ ማስተማራቸውን እንዲቀጥሉ ተደርጓል። የአብነት ትምህርትን በስፋት ካለማግኘታቸው የተነሣ ተማሪዎች ወደ ዘመናዊ ትምህርት ሲያደሉ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራን በመሥራት የአብነት ትምህርታቸውን እንዲያጠናክሩ ተደርጓል።

በመኖሪያና በማደሪያ ችግር የአኗኗር ዘይቤያቸው አስቸጋሪ በሆኑባቸው ጉባኤ ቤቶች ማደሪያ ቤት ተሠርቶ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ከፍ ማድረግ የተቻለ ሲሆን መምህራኑም የማስተማር ፍላጎት መጨመሩን መገንዘብ ተችሏል። አገልጋይ እጥረት ባለባቸው በደቡብ፣ በምሥራቅና በሌሎች አካባቢዎች አዳሪ የአብነት ት/ቤቶችን ለመሥራትና ለማስፋፋት ተችሏል።

**መጽሔተ ተልእኮ፡-** የማኅበረ ቅዱሳን አገልግሎት ለገዳማትና ገዳማውያን ያለው ፋይዳ ምንድነው?

**ዲያቆን ደረጀ፡-** በዚህ ማስተባበሪያ የማኅበሩ አገልግሎት ፋይዳው ለገዳማትና ገዳማውያን ብቻ ሳይሆን ለአብነት ትምህርት ቤቶች፣ ለአብነት ተማሪዎችና ለሊቃውንትም ጭምር ነው። ገዳማትና የአብነት ትምህርት ቤቶች ለዘመናት ይዘው ያቆዩትን መንፈሳዊና ማኅበራዊ ሀብት ለማስቀጠል፣ የኢኮኖሚ አቅጣጫቸውን ለማሻሻልና ተተኪ ትውልድን ለማፍራት እንዲያስችል ማኅበረ ቅዱሳን ባለፉት ፳፰ ዓመታት አባላቱንና ድጋፍ አድራጊ ምእመናንን በማስተባበር በየአህጉረ ስብከቱ ለሚገኙ ብዙ ገዳማትና የአብነት ት/ቤቶች የልማትና ማኅበራዊ አገልግሎት ፕሮጀክቶችን በማጥናት ከ ፬፻፰ በላይ ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ አድርጓል።

ለገዳማትና ለአብነት ትምህርት ቤቶች የአካባቢያቸውን ተፈጥሮአዊ ሀብት፣ መልክአ ምድራዊ አቀማመጥና የአየር ንብረቱን ሁኔታ በመለየት ገቢ ማስገኘት የሚችሉ የልማት ፕሮጀክቶች ተግባራዊ አድርጓል። ለምሳሌ፡- የንብ ማነብ ተግባርን ከ ፲፰ በላይ የሆኑ ፕሮጀክቶች ለ ፲፰ ገዳማት ተተግብሯል። በቀንድ ከብት ርባታ ዘርፍም በማጥናት ከ ፲፱ በላይ ለሚሆኑ ገዳማት የእንስሳት ርባታ የማድለብ ፕሮጀክት ተተግብሯል። ከ ፲፯ በላይ ለሚሆኑ ገዳማት የወፍጮ ፕሮጀክት ተተግብሯል፤ ሰባት ለሚሆኑ ገዳማትም የሽመና ፕሮጀክት ተተግብሯል።

የተፈጥሮ ሀብት እጥረት ባለበት አካባቢ ለሚገኙ ገዳማት በአቅራቢያቸው በሚገኙ ከተሞች ላይ ሰባት ለሚሆኑ ገዳማት ለአገልግሎት የሚውል ገቢ ማስገኛ ሕንፃዎችን በመገንባት ለበርካታ መናንያን የቀለብ እጥረት እስከ መፍታት ገዳማትን መታደግ ተችሏል፤ የመጠጥ ውኃ ችግር ላለባቸው ለዘጠኝ ገዳማትም እንዲሁ የመጠጥ ውኃ ፕሮጀክትን በመቅረጽ ችግሩን በዘላቂነት በመፍታት የመናንያንን ድካም መቀነስ ተችሏል።

ከገዳማት ባሻገር በአብነት ትምህርት ቤቶች ላይም በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል፤ የተለያዩ አህጉረ ስብከቶች ላይ የአብነት ትምህርት ቤቶች ማደሪያ፣ መመገቢያ፣ መማሪያ፣ ማብሰያና ንጽሕና መጠበቂያ በመገንባት ዘመኑን የዋጁ ተተኪ አገልጋዮችን ለማፍራት ታላላቅ ፕሮጀክቶች በመቅረጽ ውጤታማ ሥራዎች የተሠሩ ሲሆን በሰሜን ያሉትን ደግሞ የማጠናከሪያ ፕሮጀክቶችን ሠርቷል። በዚህ በ ፳፻፲፯ ዓ.ም ብቻ ለ ፻፸፩ ጉባኤ ቤቶች፣ ለ ፪፻፴፱ መምህራንና ለ ፳፻፪፻፴ የአብነት ተማሪዎች ወርኃዊ ድጎማ እያደረገ ይገኛል።

**መጽሔተ ተልእኮ፡-** የቅዱሳት መካናትንና የአብነት ትምህርት ቤቶች ህልውና ከማስጠበቅ አኳያ የማኅበረ ቅዱሳን አገልግሎት ለቤተ ክርስቲያንና ለሀገር ያለው ፋይዳ ምንድነው?

**ዲያቆን ደረጀ፡-** የአብነት ትምህርት ቤቶችና የገዳማት መኖር ለቤተ ክርስቲያን ህልውና መሠረታዊ ነገር ነው፤ እነርሱን ማስፋፋትና መደገፍ ቤተ ክርስቲያንን ማስፋፋት መደገፍ ነው። በአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያን ያለ ገዳማትና ያለ አብነት ትምህርት ቤቶች ተልእኮዋን መወጣት ትችላለች ማለት አይቻልም። የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ከዲያቆናት ጀምሮ እስከ ሊቃነ ጳጳሳት የሚወጡት ከአብነት ትምህርት ቤት ነውና። የአብነት ትምህርት ቤቶች መገኛቸው ደግሞ ገዳማትና አድባራት ናቸው። ስለዚህ ማኅበሩ በዚህ ማስተባበሪያ በኩል የሚያደርገው አገልግሎት ለቤተ ክርስቲያን ያለው ፋይዳ እጅግ ሰፊ ነው ማለት ይቻላል።

በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተሠሩት ሥራዎች ከላይ እንደ ተጠቀሱት ለሀገርም ልማት ናቸው። ለምሳሌ፡- ከብት ማድለብ፣ የእንስሳት ርባታ፣ ዕደ ጥበባት፣ የንብ ርባታ ሁሉ የሀገር ልማትም ጭምር ናቸው። የአብነት ትምህርት ቤቶችን፣ ተማሪዎችን እንዲሁም በገዳማት ላይ ያሉ መናንያንን አቅም ማሳደግ ማለት ሀገራችንን ማሳደግ ማለት ነው። ከዚህም በመነሣት የማኅበረ ቅዱሳን አገልግሎት ለቤተ ክርስቲያን ብቻም ሳይሆን ለሀገር ፈይዳው ከፍ ያለ ነው።

**መጽሔተ ተልእኮ፡-** የቅዱሳት መካናት ማስተባበሪያ አገልግሎት ባለድርሻ አካላት እነማን ናቸው? ምንስ ይጠቅባቸዋል?
ዲያቆን ደረጀ፡- በማኅበረ ቅዱሳን አገልግሎት ባለድርሻ አካላት የሚባሉት በርካታ ሲሆኑ እነርሱም ከጠቅላይ ቤተ ክህነት እስከ አጥቢያ ያሉ የቤተ ክርስቲያን መዋቅሮች፣ ሰንበት ትምህርት ቤቶች፣ የተለያዩ መንፈሳዊ ማኅበራት፣ እና ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን ናቸው። እነዚህ አካላት ስለ ገዳማትና የአብነት ትምህርት ቤቶች ይመለከታቸዋል፤ የሚጠበቅባቸውም እንደየድርሻቸው ነው። ለምሳሌ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ከማስተዳደር(ከመምራት)፣ ከማስፋፋት፣ ከማደራጀት፣ ጀምሮ ይመለከተዋል።
ሌሎች አካላት ደግሞ በሐሳብ፣ በገንዘብ፣ በቁሳቁስና በሌሎች ጉዳዮችም እንዲደግፉ ይጠበቅባቸዋል። በተለይ አሁን አሁን ሀገራችን ካለችበት ሁኔታ አኳያ ገዳማትና የአብነት ትምህርት ቤቶች ከዚህ በላይ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል።

**መጽሔተ ተልእኮ፡-** ማኅበረ ቅዱሳን በዚህ አገልግሎት ሂደት ተግዳሮት የሆነበት ነገር ምንድን ነው? መፍትሔውስ? ባለድርሻ አካላት በምን ማገዝ ይችላሉ?

**ዲያቆን ደረጀ፡-** አገልግሎቱ  እዚህ የደረሰው አልጋ በአልጋ በሆነ መንገድ ሳይሆን በብዙ ተግዳሮቶች መካከል አልፎ ነው። በዋናነት ደግሞ የገንዘብ እጥረት ትልቁ ተግዳሮት ነው፤ የተሠሩት ሥራዎች ጥቂት ናቸው። አብዛኞቹ ሥራዎች አሁንም ወደፊትም ድጋፍ የሚሹ ናቸው። ማኅበሩ ባለፉት ፳፩ ዓመታት ውስጥ ግንዛቤ ከመፍጠር አንሥቶ በርካታ ለውጦችን ማምጣት የቻለ ቢሆንም ከጦርነት፣ ከድርቅ፣ ከረኀብ ጋር ተያይዞ ገዳማትና የጉባኤ ቤት ተማሪዎች ቀለብ ፍለጋ ወደ ከተማ እየተሰደዱ ይገኛሉ። ስለዚህ ምእመንና ሌሎች የማኅበሩን ዓላማ የሚደግፉ ባለድርሻ አካላት ከበፊቱ በበለጠ አሁን በተሻለ መልኩ በማገዝ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል።

**መጽሔተ ተልእኮ፡-** እግዚአብሔር ይስጥልን! ቃለ ሕይወት ያሰማልን! አክብረውን ጥያቄዎቻችንን ስለመለሱልን እናመሰግናለን!
ዲያቆን ደረጀ፡- እኔም አመሰግናለሁ!

# 6. ይናገራል ፎቶው



ኸሌ ዞን ቦሌ ቀበሌ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን



ኸሌ ዞን ቦሌ ቀበሌ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን



ደቡብ ኦሞ እና አሪ ዞኖች ሀገረ ስብከት የወልባክ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን



በኮንታ ዞን ቤተ ክህነት የኦሺጋኢጋሬ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ አገልግሎት



ከፋ ሀገረ ስብከት የጎይዚ ቅዱስ ገብርኤል በተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ አገልግሎት



ከፋ ሀገረ ስብከት የጎይዚ ቅዱስ ገብርኤል በተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ አገልግሎት

## “ወደ እርሱ ቅረቡ፤ ያበራላችሁማል”
## (መዝ.፴፫፥፭)

ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት ይህንን ኀይለ ቃል የተናገረው ስለ ሕዝቅያስ ነው፡፡ ሕዝቅያስ በሁለቱ ነገድ በነገደ ይሁዳ እና በነገደ ብንያም የነገሠ ንጉሥ ነው፡፡ በኢየሩሳሌም ያሉ ሕዝቡና ካህናቱ ከንጉሡ በቀር ጣዖት እያመለኩ፣ ኀጢአት እየሠሩ እግዚአብሔርን ቢያሳዝኑ የአሶር ንጉሥ ሰናክሬም ኢየሩሳሌምን እንዲያጠፉ ታዝዞ መላእክት በነጭ በግ አምሳል እየመሩ አመጡት፡፡ ነገር ግን ሰናክሬም ለኪሶን ሲደርስ በትዕቢትና በትምክህት መልእክተኞችን ወደ ሕዝቅያስ ልኮ ከእጄ የሚያድንህ ጣዖት አለን? ብሎ እግዚአብሔርን ተሳደበ፡፡ ሕዝቅያስም ጠላቱን ይመልስለት ዘንድ ማቅ ለብሶ፣ አመድ ነስንሶ በጸሎት፣ በምህላ ወደ እግዚአብሔር ቀረበ፡፡

በዚህም ምክንያት የኢየሩሳሌምና የሕዝቦቿ ሊሆን የነበረው ጥፋት ወደ ሰናክሬምና ወደ ሠራዊቱ ተመልሷል፡፡ ስለዚህ ንጉሡ ሕዝቅያስ “ወደ እግዚአብሔር በመቅረብ ከመከራ እንደ ዳነ እናንተም ትድናላችሁ” ለማለት ነቢዩ ዳዊት በሕዝቅያስ ተገብቶ (ስለ ሕዝቅያስ ሆኖ) ኀሠሥክዎ ለእግዚአብሔር ወተሰጥዎኒ ወእምኵሉ ምንዳቤየ አድኀነኒ ቅረቡ ኀቤሁ ወያበርህ ለክሙ እግዚአብሔርን ፈለግሁት፤ እርሱም መለሰልኝ፤ ከመከራዬም ሁሉ አዳነኝ፡፡ ወደ እርሱ ቅረቡ፤ ያበራላችሁማል” አለ፡፡
ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ምንድን ነው?

............እግዚአብሔር ከምልአቱ የተነሣ በሲኦል አለ፤ በእርሱ ዘንድ ግን ጨለማ የለም፡፡ ረድኤቱም በሲኦል አይገኝም፡፡ የሌለበት ቦታ የለም፤ ሆኖም ግን ኀጢአትን የሚጸየፍ አምላክ ነውና ኀጢአት ባለበት በዚያ በረድኤት ይገለጥ ዘንድ ፈቃዱ አታገብረውም፡፡ እርሱ በሁሉ እየኖረ ሁሉንም አይቀርብም፡፡ በሁሉ እያለ የማይፈቅደውን ይርቃል፤ በሁሉ እያለም የሚወደውን ይቀርባል፡፡ ከምልአቱ በጸጋ፣ በበረከትና በረድኤት ይገለጣል፤ ከምልአቱም ጸጋውን፣ ረድኤትና በረከቱን ያርቃል፡፡ ይህንን ከእርሱ በቀር ሊያደርገው የሚችል ፍጥረት የለም፡፡ ፍጥረት በምልአት ከወደደው ቦታ ደርሶ በወደደው መታየትና መገለጥ አይችልምና፡፡ ታዲያ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ምንድን ነው? ነቢዩ ወደ እርሱ ቅረቡ ያበራላችሁማል ብሎ የነገረንስ ለምንድን ነው? ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ማለት የእግዚአብሔርን ሕግ መጠበቅ፣ እርሱን ማምለክና ፈቃዱን በመፈጸም የእርሱ ማደሪያ መሆን ነው፡